በብስለት ማደግ

የመንፈሳዊ ሕይወትን ዕድገት ማነቆ አሸቀንጥሮ በመጣል በክርስቶስ ስለማደግ

ጽሑፍ፡- በዋረን ደብልዩ ዊርዝቢ
ትርጉም፡- በጌቱ ግዛው
እርማት፡- በፈቃዱ ገብሬና በተስፋዬ መስፍን

1ኛ እትም 1988 ዓ.ም
2ኛ እትም 1989 ዓ.ም
3ኛ እትም 1995 ዓ.ም

Copyright © 2002 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia. Originally published in English under the title of BE MATURE. Copyright © 1978 by SP Publications, Inc. Cook Communications Ministries, 4050 Lee Vance View, Colorado Springs, Colorado 80918 USA. All rights reserved.



መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ.ቁጥር 127
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

መግቢያ

ብዙ ሰዎች በዕድሜ የመግፋታቸውን ያህል ሲያድጉ አይታዩም። በዕድሜ በመግፋትና በብስለት መካከል እጅግ ሰፊ ልዩነት አለ። በፅንሰ አሳብ ደረጃ በዕድሜ እየገፋን በሄድን ቁጥር በብስለትም እየጨመርን መሄድ ቢኖርብንም፥ ብዙ ጊዜ ግን ይህ ፅንሰ አሳብና ተግባራት አይገናኙም።

ይህ ባለመሆኑም በግል ሕይወት በቤተሰብና በቤተ ክርስቲያን ሁሌ ችግር ይከሰታል። ከመጋቢነት አገልግሎቴ በዚህ አኳያ የሚፈጠረው ችግር ከማንኛውም እንደሚበልጥ ተረድቼአለሁ። ክርስቲያኖች በሕይወታቸው እያደጉ በሚሄዱበት ጊዜ ተሸናፊ ከመሆን ይልቅ ድል አድራጊዎች ይሆናሉ።

የያዕቆብ መልእክት የተጻፈው የመንፈሳዊ ሕይወት ብስለትን ምንነት እንድናውቅና እንዴት እንደምናገኘው ተረድተን በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን እንድንሄድ ነው። «ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ...» (ያዕ. 1፡4)። ይህንን አሳብ ጄ.ቢ. ፊሊፕስ የተባሉት የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ በማለት በጥሩ ሁኔታ አስቀምጠውታል፡- «... እራሳችሁን የበሰለ ባሕርይ የሚያንጸባርቁ ጽኑዓንና ደካማ ነጥቦች የሌላቸው ሰዎች ሆናችሁ ታገኛላችሁ።»

ይህ ቀለል ያለ በመጽሐፍ ቅዱስ ገለጣ ላይ የተመሠረተ ጥናት ወደዚህ ግብ ለመድረስ እንደሚረዳችሁ እምነቴ ነው።

ዋረን ዌርዝቢ

ማውጫ

1. የዕድገት ጊዜ 1
2. መከራን ወደ ድል መለወጥ 13
3. ፈተናን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል . . . 26
4. እራስን ከማታለል እንቆጠብ 38
5. ሀብታም ሰው፣ ድሀ ሰው 51
6. ሐሰተኛ እምነት 63
7. በዓለም ላይ አነስተኛ ሆና ከፍተኛ ችግርን የምትፈጥር ነገር 75
8. ጥበብ የት እንደምትገኝ 88
9. ጦርነቶች እንዴት ያከትማሉ? 101
10. አስቀድመህ ዐቅድ 113
11. ገንዘብ ይናገራል 125
12. የትዕግሥት ኃይል 136
13. እንጸልይ 147

ያዕቆብ 1:1

«የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ ለተበተኑ ለአሥራ ሁለቱ ወገኖች ሰላም ለእናንተ ይሁን።»

የዕድገት ጊዜ

አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ማጥናት መጀመር ለአንድ ጉዞ እንደ መዘጋጀት ነው። የምትሄዱት ወዴት እንደሆነና በዚያ ስፍራ ስለምታዩአቸው የተለያዩ ነገሮች ለማወቅ ትጓጓላችሁ። እኔና ባለቤቴ ወደ እንግሊዝ ሀገር ለጉብኝት ለመሄድ በምንዘጋጅበት ወቅት ሀገሪቱን ለሚጎበኙ ሰዎች ይጠቅም ዘንድ መረጃዎችን የያዘውን የጉዞ መጽሐፍ በማንበብና መልክዓ-ምድር ጠቋሚ (ካርታዎችን) በማጥናት ብዙ ሰዓታትን አሳለፍን። በስፍራው በደረስን ጊዜ በጉብኝታችን መጀመሪያ ካሰብነው ይልቅ እጅግ ተደሰትን፤ ምክንያቱም የምንፈልገውን ነገርና እንዴት እንደምናገኘውም በሚገባ አስቀድመን አውቀን ነበር።

የያዕቆብን መልእክት ስናጠና ለሚከተሉት አራት አስፈላጊ ጥያቄዎች መልስ መስጠት አመቺ ይሆናል።

ያዕቆብ ማነው?

ያዕቆብ እራሱን ሲያስተዋውቅ «የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ...» ይላል (ያዕቆብ 1፡1)። ይህ ስም በብዙዎች ዘንድ የታወቀ ስም ነው። በብሉይ ኪዳን ታላቅ ስም ከነበረው ያዕቆብ የተባለው ሰው ስም ጋር ተመሳሳይ ነው። በአዲስ ኪዳን ታሪክ በዚህ ስም የሚጠሩ ጥቂት ሰዎች ነበሩ።

የዘብዴዎስ ልጅና የዮሐንስ ወንድም የሆነው ያዕቆብ በዚህ ስም በመታወቅ ተቀዳሚ ስፍራ ከነበራቸው ሰዎች አንዱ ነው። ይህ ሰው ዓሣ አጥማጅ ሲሆን ደቀ መዝሙሩ እንዲሆን ክርስቶስ የጠራውም በዚህ ዕለታዊ ተግባሩ ላይ ሳለ ነበር (ማቴ. 4፡17-22)። ክርስቶስ ይህንን ደቀ መዝሙርና ወንድሙን «የነጎድጓድ ልጆች» የሚል ቅፅል ስም አውጥቶላቸው ነበር። ምክንያቱም ቁጡዎች ነበሩ (ማር. 3፡17 ና ሉቃስ 9፡51-56 አንብብ)። ያዕቆብ በ44 ዓ.ም. በሄሮድስ እጅ ተገደለ። ስለዚህ ከደቀ መዛሙርት መካከል ሕይወቱን ለክርስቶስ የሠዋ የመጀመሪያው ሰማዕት ነው። (የሐዋ. 12፡1-2)

የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፥ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ነበር። ሆኖም ስለ እርሱ የተገለጠው በጥቂቱ ነው (ማቴ. 10፡3፤ የሐዋ. 1፡13)። ሌዊ የተባለው ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ማቴዎስም የእልፍዮስ ልጅ እንደሆነ

ስለተጠቀሰ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ማቴዎስና ያዕቆብ ወንድማማቾች ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ያስባሉ። የምናጠናውን የያዕቆብን መልእክት የጻፈው ይህ ሰው ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክት አንዳችም ነገር የለም።

የደቀ መዝሙሩ የይሁዳ አባት ያዕቆብ፡- የያዕቆብ ልጅ የተባለው ከአስቆሮቱ ይሁዳ የተለየ መሆኑን ለማሳየት ነው (ሉቃ. 6፡16)። ስለዚህኛው ያዕቆብ የተገለጠውና የምናውቀው ነገር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው።

የጌታ ወንድም ያዕቆብ፡- ከሁሉም ይልቅ ይህን መልእክት የጻፈው ይህኛው ያዕቆብ እንደሆነ መገመት ይቻላል። የጌታ ወንድም ቢሆንም እንኳ እራሱን በዚህ መንገድ አላስተዋወቀም። ነገር ግን በታላቅ ትሕትና እራሱን «የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ...» በማለት ጠራ። ኢየሱስ ወንድሞችና እኅቶች እንደነበሩት በማቴ. 13፡55-56፤ በማርቆስ 6፡3 እንመለከታለን። ከወንድሞቹም አንዱ ያዕቆብ ነበር። (የኢየሱስ ወንድሞችና እኅቶች ከኢየሱስ ጋር ያላቸው ግንኙነት በአንድ ወገን ብቻ ማለትም በማርያም እናትነት ነው። ኢየሱስ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ስለሆነና የቀሩት ወንድሞቹና እኅቶቹ ደግሞ አባታቸው ዮሴፍ ስለሆነ በአባት አይገናኙም ማለት ነው።)

ያዕቆብና የቀሩት የኢየሱስ ወንድሞች ኢየሱስ በምድር ላይ እያለ በእርሱ አላመኑም ነበር (ዮሐ. 7፡1-5ና ማርቆስ 3፡31-35)። በሐዋርያት ሥራ 1፡14 ላይ ግን ለጸሎት በአንድነት ተሰብስበው ከነበሩት ደቀ መዛሙርት ጋር የኢየሱስ ወንድሞች እንደነበሩ እንመለከታለን። የኢየሱስን ወንድሞች ካለማመን ወደማመን ያመጣቸው ነገር ምንድነው? በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡7 ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለያዕቆብ እንደተገለጠለት ያመለክታል። ትንሣኤው ያዕቆብን ኢየሱስ እውነተኛው አዳኝ እንደሆነ እንዲያምን አደረገው። ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ለቀሩት ወንድሞቹ ስለ ኢየሱስ የተገነዘበውን እውቀት አካፈላቸው።

ያዕቆብ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነ። በገላ. 2፡9 ላይ ጳውሎስ «አዕማድ» ብሎ ከጠራቸው መካከል አንዱ ያዕቆብ ነው። በሐዋርያት ሥራ 15 ላይ የምንመለከተውን የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የመራው ያዕቆብ ነበር። ጴጥሮስ በእግዚአብሔር ተአምር ከእስር ቤት በወጣ ጊዜ መልእክት የላከው ለያዕቆብ ነበር (የሐዋ. 12፡17)። ጳውሎስ ኢየሩሳሌምን በጎበኘ ጊዜ ከአሕዛብ የተሰበሰበውን «የፍቅር ስጦታ»ና ሰላምታ ያቀረበው ለያዕቆብ ነበር (የሐዋ. 21፡18-19)።

ስለ ያዕቆብ አሟሟት በመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘገበ ነገር የለም። ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ግን በ62 ዓ.ም. እንደተገደለ ይናገራል። ስለ አገዳደሉ የሚናገረው ታሪክ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ፈሪሳውያን ያዕቆብ ስለ ክርስቶስ በሚሰጠው ምስክርነት እጅግ ስለጠሉት ከቤተ መቅደስ ቁልቁል ወርውረው ከጣሉት በኋላ በዱላ ቀጥቅጠው እንደገደሉት ነው። ያዕቆብ በሚገደልበት ጊዜ ልክ እንደ አዳኙ እንደ ኢየሱስ ለገዳዮቹ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ብሎ እንደጸለየ ይህ ታሪክ በተጨማሪ ይናገራል።

ያዕቆብ ምን ዓይነት ሰው ነበር? በዚያ አጭር ጊዜ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን የቻለ እጅግ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ሕይወት የነበረው ሰው ነበር ማለት ነው። በሐዋ. 15 ላይ በተካሄደው ጉባኤ የተለያየ አቋም የነበራቸው መሪዎች በሙሉ አሳባቸውን እንዲገልጹ ካደረገ በኋላ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ግጠቃለያ በመስጠት ሰላምን ማውረዱ የነበረውን መንፈሳዊ አቋም ያሳያል። ያዕቆብ ሚስት እንደነበረችው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 9፡5 ላይ ከተናገረው አሳብ እንመለከታለን። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ደግሞ የጸሎት ሰው እንደነበረ ይናገራል። በመልእክቱ ላይ ስለ ጸሎት የሰጠው ትኩረት ይህንን የሚያመለክት ነው። ለረጅም ሰዓት በጸሎት ያሳልፍ ስለ ነበር ጉልበቶቹ እንደ ግመል ጉልበቶች ጠንካሮች እንደነበሩ ይነገራል።

ያዕቆብ በሙሴ ሕግ ባህል ያደገ አይሁዳዊ ስለነበረ አይሁዳዊ ወግ አጥባቂነትን (ሕጋዊነትን) በመልእክቱ ውስጥ እንመለከታለን። (በተጨማሪም ከሐዋ. 21፡18-40 ያዕቆብ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ሕግን የሚያጠብቁ ክርስቲያኖችን ጸጥ ለማሰኘት የጳውሎስን እርዳታ እንደጠየቀ አስተውል። በያዕቆብ መልእክት ውስጥ 50 ትእዛዞች ይገኛሉ። ያዕቆብ ትእዛዞቹን በቀጥታ ሰጠ እንጂ ቢደረግ መልካም ነው በሚል ስሜት አስተያየት አላቀረበም። በመልእክቱ ውስጥ የብሉይ ኪዳንን አሳብ የሚያስታውሱ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም ከብሉይ ኪዳን በቀጥታ የጠቀሰው ግን አምስት ጊዜ ብቻ ነው።

ያዕቆብ በኢየሱስ ከማመኑ በፊት እንኳ ኢየሱስ ለሚያስተምረው ትምህርት ትኩረትን ሰጥቶ ነበር። በመልእክቱ ውስጥ ከጌታችን ንግግሮች ጋር በተለይ ደግሞ ከተራራው ስብከት ጋር የሚመሳሰል በርካታ ነገሮችን እናገኛለን። የሚከተሉትን ክፍሎች አወዳድር።

ያዕቆብ 1:2 - ከማቴዎስ 5:10-12

ያዕቆብ 1:4 - ከማቴዎስ 5:48

ያዕቆብ 1:5 - ከማቴዎስ 7:7-12

ያዕቆብ 1:22 - ከማቴዎስ 7:21-27

ያዕቆብ 4:11-12 - ከማቴዎስ 7:1-5

ያዕቆብ 5:1-3 - ከማቴዎስ 6:19-21

ያዕቆብ በኢየሩሳሌም የነበረችዋን ቤተ ክርስቲያን የመራው እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ እንደ ነበር አስተውል። ጊዜው የሽግግር ወቅት ነበር። እንደዚህ ዓይነቱ ጊዜ ደግሞ በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ነው። በኢየሩሳሌም በርካታ ሕግ አጥባቂ ክርስቲያኖች ነበሩ (የሐዋ. 21:20)። ቤተ መቅደሱና በውስጡ የሚሰጡ አገልግሎቶች እንደ ወትሮው እየተካሄዱ ነበር። ደግሞም የእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል በሙላት ገና አልተገለጠም ነበር። ሮሜን፥ ገላትያንና ዕብራውያንን በምናነብበት ጊዜ በዚያን ዘመን በነበሩ ክርስቲያኖች ላይ ለመፍረድ እንፈተን ይሆናል። ነገር ግን ልንፈርድባቸው አይገባም። በክርስቶስ አምነው የዳኑ ሰዎች ቢሆኑም እንኳ በሕግ ጥላ ሥር ሆነው ወደ እግዚአብሔር ጸጋ ደማቅ ብርሃን ገና እየወ ጡ ነበር። በጳውሎስና በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል የመንፈሳዊ እውቀትና ልምምድ እንዲሁም የዕድገት ልዩነት ቢኖርም ውድድር ግን አልነበረም (ገላትያ 2:1-10)።

ያዕቆብ መልእክቱን የጻፈው ለማን ነበር?

«... ለተበተኑ ለአሥራ ሁለቱ ወገኖች ሰላም ለእናንተ ይሁን» (ያዕቆብ 1:1)። ያዕቆብ ይህን መልእክት የጻፈው ከኢየሩሳሌም ራቅ ብለው ለሚኖሩ አይሁዶች ነበር። «ለአሥራ ሁለቱ ወገኖች» የሚለው ቃል የአይሁድ ዘር የሆነው የእስራኤል ሕዝብ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም (የሐዋ. 26:7)። በዚያን ጊዜ ብዙ አይሁዶች የሚኖሩት ከተስፋይቱ ምድር ውጪ መሆኑ የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት በማሽቆ ልቆል ላይ እንደሆነ ማስረጃ ነው። እግዚአብሔር እነርሱን መበተን ነበረበት (ዘዳግ. 4:25-49)። ጴጥሮስ በበዓለ ኃምሳ ቀን ያቀረበውን መልእክት ያሰማው ከበርካታ የተለያዩ ዘሮች ለመጡ ታላቅ የአይሁድ ሕዝብ ክምችት መሆኑን እንመለከታለን (የሐዋ. 2:9-11)።

ያዕቆብ ይህን መልእክት የላከው ለክርስቲያን አይሁዶች ነው። በዚህ መልእክት ውስጥ 19 ጊዜ ያህል «ወንድሞች» እያለ

ይጠራቸዋል። ይህም «በሥጋ ወንድሞቹ» ወይም አይሁዳዊ ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን «በጌታ ወንድሞች» መሆናቸውንም የሚያመለክት ነው። ያዕቆብ በአዲስ ልደት መሠረታዊ ትምህርት ላይ ያለው አሳብ በጣም ግልጽ ነው (ያዕቆብ 1፡18)። ያዕቆብ በጎብረቱ ውስጥ የሌሉ ከፋ ሰዎችንም በመልእክቱ ውስጥ የሚጠቅስበት ጊዜ አለ (ለምሳሌ በያዕቆብ 5፡1-6 ባለጠጎችን ይጠቅሳል)። ነገር ግን ይህንንም እንኳ ያደረገው መልእክቱን የሚጽፍላቸው የዳኑ አይሁዶችን ለማስተማርና ለማበረታታት ነበር።

በያዕቆብ 1፡1 ላይ የምናገኘው «ለተበተኑ» የሚለው ቃል በጣም አስደናቂ ትርጉም ያለው ቃል ነው። በአጭሩ «ተሰራጭተው ያሉ» ማለት ነው። ይህ ቃል ከኢየሩሳሌም ራቅ ብለው በተለያዩ ስፍራዎች ተበትነው የሚኖሩትን አይሁድ የሚያመለክት ነው። ነገር ግን አዲስ ኪዳን መጀመሪያ የተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ የዚህ ቃል ትርጉም «ዘርን የመዝራት» አሳብ ያለው ነው። የአይሁድ አማኞች በመጀመሪያው የስደት አውሎ ነፋስ በተበተኑ ጊዜ (የሐዋ. 8፡ 1 እና 4) በብዙ ስፍራ ዘር የተዘራበት ወቅት ነበር። የዚህ ዘር አብዛኛው ክፍል ፍሬ አፍርቷል (የሐዋ. 11፡19-26)።

በሮም መንግሥት የግዛት ክልል ውስጥ ተበትነው የነበሩ ክርስቲያን አይሁዶች የራሳቸው የሆነ በርካታ ችግሮችና ፍላጎቶች ነበሩአቸው። አይሁዶች በመሆናቸውም በአሕዛብ የተጠሉ ነበሩ። ክርስቲያን አይሁዶች በመሆናቸው ደግሞ በራሳቸው አገር ሰዎች የተጠሉ ነበሩ። ይህ መልእክት ከእነዚህ ክርስቲያኖች አብዛኛዎቹ ድሆች እንደነበሩና እንዲያውም አንዳንዶቹ በሀብታሞች ይጨቆኑ እንደነበሩ ያመለክታል።

ያዕቆብ ይህን መልእክት የጻፈው ለምን ነበር?

እያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን መልእክት የራሱ የሆነ ልዩ ግብ፥ ዓላማና መልእክቱ የሚላክለት አንድ የተወሰነ አድራሻ አለው። ጳውሎስ የሮሜ መጽሐፍን የጻፈው የሮሜ ክርስቲያኖችን ለመጎብኘት ስላለው ዕቅድ ሊያዘጋጃቸው ነበር። የ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት የተጻፈው በቆሮንቶስ የምትገኘዋ ቤተ ክርስቲያን የነበሩባትን አንዳንድ ችግሮች ለማስተካከል ነበር። የገላትያ መልእክት የተጻፈው የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናትን ከሕጋዊነትና ከሐሰት ትምህርት እንዲጠበቁ ለማስጠንቀቅ ነበር።

የያዕቆብን መልእክት ስታነብ እነዚህ የአይሁድ ክርስቲያኖች በግል ሕይወታቸውና በቤተ ክርስቲያን ባላቸው ጎብረት አንዳንድ ችግሮች እንደነበሩባቸው ትገነዘባለህ። የመጀመሪያው በከባድ ፈተናዎች ውስጥ

እያለፉ መሆናቸው ነበር። ደግሞም ኃጢአትን ለማድረግ የሚፈተኑበት ሁኔታም ገጥሟቸው ነበር። አንዳንድ አማኞች ለሀብታሞች ያገለግሉ ነበር። ሌሎች ደግሞ በሀብታሞች ይበዘበዙ ነበር። ምእመናኑም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የሥልጣን ቦታዎችን በተለይም የማስተማር ኃላፊነትን ለመያዝ እርስ በርስ በውድድር መንፈስ ተጠምደው እናገኛቸዋለን።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከነበሩት ዋና ዋና ችግሮች አንዱ ብዙ ሰዎች የሚያምኑትን የክርስቲያን ኑሮ ሆነው አለመገኘታቸው ነበር። በተጨማሪ በጉባኤ መካከል መከፋፈል እስከሚያስከትል ድረስ አንደበትን አለመቆጣጠር ከፍተኛ ችግር ሆኖ እንደነበር እንመለከታለን። ዓለማዊነት ደግሞ ሌላው ችግር ነበር። ከቤተ ክርስቲያን አባላት አንዳንዶቹ ለእግዚአብሔር ቃል ባለመታዘዛቸው በሥጋቸው ታምመው እንደነበር፥ ሌሎች ደግሞ ከመንገዳቸው ስተው ከጌታና ከቤተ ክርስቲያን እንደሸሹ እንመለከታለን።

የእነዚህን ችግሮች ዝርዝር ስንመለከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልንመረምር ይገባል፦ እነዚህ ችግሮች በአሁኑ ጊዜ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከሚያጠቋት ችግሮች ብዙ የተለዩ ናቸውን? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት መከራን የሚቀበሉ ሰዎች የሉምን? የሚናገሩትና የሚኖሩት ጨርሶ የተለያዩ አባላት የሉንም? ዓለማዊነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ችግር አይደለምን? አንደበታቸውን መቆጣጠር የማይችሉ ክርስቲያኖች የሉምን? እንግዲህ እነዚህን ነገሮች አስመልክቶ ያዕቆብ የሚናገረው እጅግ ወቅታዊ ስለሆኑ ጉዳዮች እንደሆነ እንመለከታለን።

ያዕቆብ ያለምክንያት ይህን ትንተና አላቀረበም። እነዚህ ችግሮች ሁሉ የጋራ ምክንያት አላቸው። ይኸውም መንፈሳዊ እንጭጭነት (ያለመብሰል) ነው። በቀላል አነጋገር እነዚህ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወት አላደጉም። የዚህን መልእክት መሠረታዊና ዋና አሳብ ምን እንደሆነ ለመ መልከት የሚረዳን ፍንጭ እናገኛለን። ይህም የክርስትና ሕይወት ምልክት የሆነው መንፈሳዊ ብስለት ነው። ያዕቆብ «ፍጹም» የሚለውን ቃል ብዙ ጊዜ ይጠቀምበታል። የቃሉ ትርጉም «የበሰለ፤ ምሉዕ» ማለት ነው (1:4፥ 17፥ 25፤ 2:22፤ 3:2 ተመልከቱ)። ያዕቆብ «ፍጹም ሰው» (3:2) ሲል ኃጢአት የሌለበት ማለት አይደለም። ነገር ግን የበሰለ፥ ሚዛናዊ ሕይወት ያለው፥ ያደገ ማለቱ ነው።

ዛሬም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ መንፈሳዊ ብስለት ነው። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የአዋቂዎች ማሠልጠኛ ቦታ መሆን ሲገባቸው የሕፃናት መዋያ ስፍራዎች ናቸው። አባሎቻቸው እንደሚገባ ካለመብሰላቸው የተነሣ የሚያስፈልጋቸውን ጠንካራ መንፈሳዊ ምግብ ለመመገብ አይችሉም፤ ስለዚህ ገና ወተት መመገብ ያስፈልጋቸዋል (ዕብ. 5፡11-14)። ያዕቆብ የጠቀሳቸውን ችግሮች ስንመለከት ችግሮቹ ሁሉ የትናንሽ ልጆች ባሕርያት መሆናቸውን በግልጽ ትመለከታለህ።

- በችግሮች ውስጥ ለመታገሥ ያለመቻል፤ 1፡1-4
- እውነትን ቢናገሩም በተናገሩት እውነት ያለመኖር፤ 2፡14-26
- አንደበትን ያለመግታት፤ 3፡1-18
- ጠብና ቅናት፤ 4፡1-17
- ቁሳቁሳዊ ነገሮችን ማግበስበስ 5፡1-12

ከ 25 ዓመታት በላይ አገልግሎት በኋላ በአብያተ ክርስቲያናችን ውስጥ ትልቁ ችግር መንፈሳዊ እንጭጭነት (ያለመብሰል) እንደሆነ ተረድቻለሁ። እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሠሩ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበሰሉ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ይፈልጋል። ብዙ ጊዜ ግን የሚገኙት እርስ በርስ እንኳ በአንድነት እንዴት መኖር እንዳለባቸው የማያውቁ ትናንሽ ልጆች ናቸው።

በዚህ መልእክት አምስት ምዕራፎች የበሰሉ ክርስቲያኖች የሚታወቁባቸውን አምስት ምልክቶች ያቀርባሉ። ያዕቆብ የመልእክቱን አሳብ ቅደም ተከተል በዚህ መንፈሳዊ ብስለት በሚባል ዋና አሳብ ላይ አዘጋጅቶ ቢሆን ኖሮ በሚከተለው መልክ ያቀርበው ነበር፦

ዋና አሳብ፡- መንፈሳዊ ብስለት

መሪ ጥቅስ፡- ያዕቆብ 1፡4

በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ክርስቲያን ምልክቶች፡-

1. በፈተና ውስጥ ታጋሽ ነው- ምዕ. 1
   ሀ. ከውጭ የሚመጡ መከራዎች- 1፡1-12
   ለ. ከውስጥ የሚነሡ ፈተናዎች- 1፡13-27
2. እውነትን በተግባር ላይ ያውላል- ምዕ.2
   ሀ. እምነትና ፍቅር- 2፡1-13

ለ. እምነትና መልካም ሥራዎች- 2፡14-26

3. አንደበቱን የመግታት ኃይል አለው - ምዕ. 3

ሀ. ተግሣጽ ምክር - 3፡1-2

ለ. ለማብራሪያ የሚሆኑ መግለጫዎች - 3፡3-12

ስድስት የአንደበት ገለጻዎች

ሐ. መተግበር - 3፡13-18

4. ለላምን የሚፈጥር ረብሸኛ ያልሆነ ነው- ምዕራፍ 4

ሀ. ሦስት ጦርነቶች- 4፡1-3

ለ. ሦስት ጠላቶች- 4፡4-7

ሐ. ሦስት ግሣጼዎች- 4፡8-17

5. በችግሮች ውስጥ ሲሆን በጸሎት የሚተጋ ነው - ምዕራፍ 5

ሀ. የኢኮኖሚ ችግሮች- 5፡1-9

ለ. የሥጋ ችግሮች- 5፡10-16

ሐ. የብሔር ችግሮች- 5፡17-18

መ. የቤተ ክርስቲያን ችግሮች- 5፡19-20

ይህንን መልእክት የምናጠናበት ሌሎች መንገዶች እንደሚኖሩ የተረጋገጠ ነው። ይህ ግን ይህን መልእክት የምንመለከትበት አንዱ መንገድ ነው። በመልእክቱ ውስጥ የሚገኙ ምዕራፎችን አንድ በአንድ በምናጠናበት ጊዜ ስለ መንፈሳዊ ብስለትና ወደዚህ ብስለት እንዴት መድረስ እንደሚቻል የሚሰጥ ትንተና ላይ ትኩረት እናደርጋለን።

ከዕብራውያን መልእክት ዋና ዋና አሳቦች አንዱ መንፈሳዊ ፍጹምነት ነው፤ ከእርሱ ቀጥሎ ስለ መንፈሳዊ ፍጹምነት የሚናገረው ደግሞ የያዕቆብ መልዕክት ነው። በዕብራውያን መልእክት ውስጥ «ፍጹም» የሚለው ቃል ቢያንስ 14 ጊዜያት ያህል ይገኛል። መሪ ጥቅሱ ዕብራውያን 6፡1 ነው። «... ወደ ፍጻሜ እንሂድ» ይህም ማለት ወደ «መንፈሳዊ ብስለት» መድረስ ማለት ነው። የዕብራውያን ጸሐፊ በክርስቶስ ስለሚገኘው ፍጹም ደኅንነት ይገልጻል። ያዕቆብ መልዕክቱን ለሚያነብቡ ሰዎች በዚህ ፍጹም ደኅንነት ላይ እንዲገነቡና ወደ ብስለት እንዲመጡ ይመክራቸዋል። ያለ ክርስቶስ ፍጹማዊ ተግባር የአማኞች ፍጹምነት ሊገኝ አይችልም።

በዚህ ጥናት እንደሚገባ መጠቀም የምንችለው እንዴት ነው?

የዚህ ጥናት ዋና አሳብ መንፈሳዊ ብስለት እንደመሆኑ መጠን በክርስትና ሕይወታችን የት ቦታ እንዳለን እራሳችንን ልንመረምር ይገባናል።

በመጀመሪያ ደረጃ ዳግም መወለዳችን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። መንፈሳዊ ልደት ሳይኖር መንፈሳዊ ብስለት ሊኖር አይችልም። ያዕቆብ ስለ መንፈሳዊ ልደት የተናገረው ገና በመልእክቱ መጀመሪያ ላይ ነው። «ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን» (ያዕቆብ 1፡18)። 1ኛ ጴጥ. 1፡23 ከዚህ ጥቅስ ጋር በአንድነት የሚሄድ አሳብ ያለው ጥቅስ ነው። «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።»

አንድ ሕፃን ሁለት ወላጆች እንዳሉት ሁሉ መንፈሳዊ ሕፃንም ሁለት ወላጆች አሉት። እነርሱም የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ናቸው። የእግዚአብሔርን ቃል የሚያመለክቱ ሁለት ጥቅሶችን ቀደም ብለን ተመልክተናል። ዮሐንስ 3፡5-6 ደግሞ የእግዚአብሔርን መንፈስ ይጠቅሳል። (በእኔ አመለካከት በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው «ከውኃ መወለድ» የሚለው ቃል በአካል ስለ መወለድ የሚናገር ነው። ሕፃናት ሁሉ «ከውኃ ተወልደዋል» በዮሐንስ 3፡5 ላይ ኒቆዲሞስ የሚያስበው በአካል ስለ መወለድ ነበር።)

እንግዲያውስ ሰው «ዳግም የሚወለደው» እንዴት ነው? የእግዚአብሔር መንፈስ እና የእግዚአብሔር ቃል በክርስቶስ ወዳመነው ኃጢአተኛ ልብ ይገባና አዲስ ሕይወትን ያመነጫል። ይህ ተአምር ነው። መንፈስ ቅዱስ ኃጢአተኛውን ወቅሶ ለማሳመንና አዳኙ ማን እንደሆነ ለማሳየት በቃሉ ይጠቀማል። ደኅንነትን ያገኘው በእምነት ነው (ኤፌ. 2፡8-9)፤ እምነት ደግሞ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ቃል ነው (ሮሜ 10፡17)።

ዳግም የተወለድን ከሆነ ከያዕቆብ መልእክት የሚገኘውን ከፍተኛ ጥቅም በሙሉ ለማግኘት ሁለተኛው ቁም ነገር በታማኝነት በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን እራሳችንን መመርመር ነው። ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ቃል በመስተዋት ይመስለዋል (ያዕቆብ 1፡22-27)። ቃሉን በምናጠናበት ጊዜ መለኮታዊ በሆነው መስተዋት ምን እንደምንመስል እራሳችንን እናያለን። ያዕቆብ ስለዚህ ጉዳይ የሚያስጠነቅቀን ግን ስላየነው ነገር ታማኝ መሆን እንዳለብን እንጂ

ምስላችንን ብቻ በመስተዋቱ አይተን ዝም ብለን መሄድ እንደሌለብን ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ በመስተዋት ውስጥ እራሱን ስለተመለከተው ስለ አንድ ያልሰለጠነ የጥንት ሰው ሰምተህ ይሆናል። ስለተመለከተው ነገር በጣም ከመደናገጡ የተነሣ መስተዋቱን ሰበረው። ብዙ ክርስቲያኖች እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ስሕተት ይፈጽማሉ። በእራሳቸው ላይ መፍረድ ሲገባቸው ሰባኪውን ወይም ትምህርቱን ይተቻሉ።

ይህም ወደ ሦስተኛው ቁም ነገር ይመራናል። ዋጋው ምንም ያህል ይሁን እግዚአብሔር ያስተማረንን ነገር ልንታዘዝ ይገባል። «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ፡ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ» (ያዕቆብ 1፡22)። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሳተፍ፥ ትምህርቱን ለሌሎች ማካፈልና በትምህርቱ ላይ መወያየት ቀላል ነው። የተማርነውን ነገር በዕለታዊ ሕይወታችን ተግባር ላይ ማዋል ግን እጅግ የበለጠ አስቸጋሪ ነው። በረከት የሚገኘው የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ሳይሆን በመታዘዝ ነው። ለመታዘዝ ፈቃደኞች እስካልሆንን ድረስ ጌታ ሊያስተምረን አይችልም(ዮሐ. 7፡17)።

አራተኛው ቁም ነገር ለተጨማሪ ፈተናና ችግር መዘጋጀታችን ነው። ስለ መንፈሳዊ ዕድገት በምንተጋበት ጊዜ ጠላትም ተግቶ ይቃወመናል። ምናልባት ብዙ ትዕግሥት ያስፈልግህ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ብዙ መከራን ለመቀበል ተዘጋጅ። «መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ» እናውቃለንና (ሮሜ 5፡3)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ እውነተኛ ፈተናዎች የሚመጡት በሕይወት ትምህርት ቤት ውስጥ እንጂ በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ አይደለም።

በቅርቡ ትዕግሥተኛ ለመሆን ከፍተኛ ፍላጎት ስላደረበት ስለ አንድ ሰው አነበብኩ። በዚህኛው የሕይወቱ ገጽታ ማለትም በትዕግሥት እንዳላደገ ያውቅ ነበርና ለማደግ አጥብቆ ፈለገ። በቅን ልብ እንዲህ ብሎም ጸለየ፡- «ጌታ ሆይ በትዕግሥት እንዳድግ እርዳኝ። በዚህ ጉዳይ በሕይወቴ የበለጠ ራስን መግዛት እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ» አለ። በዚያን ቀን ጠዋት ወደ ሥራ የሚሄድበት ባቡር አመለጠውና የሚቀጥሉትን 50 ደቂቃዎች በመጠበቂያው ስፍራ ላይ ሆኖ በደረሰበት ነገር እያዘነና እያጉረመረመ አሳለፈ። የሚቀጥለው ባቡር እርሱ ወደ አለበት ከተማ እንደደረሰ ሰውዬው ምን ያህል ለመረዳት የዘገየ ሰነፍ መሆኑን ተገነዘበ። ስለዚህም እንዲህ አለ፡- «እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ እንድሆን አንድ ሰዓት ያህል ሰጠኝ። እኔ ግን በትዕግሥት የለሽነቴ ቆየሁ»።

በዚህ ጥናትህ ውስጥ የጀመርከውን ነገር መቀጠል አደገኛ መስሎ የሚታይህ ጊዜ ሊመጣ ይችላል። ሰይጣን ሊያበሳጭህና ነገሮችን ሁሉ ለአንተ አስቸጋሪ በማድረግ ወደ ኋላ ለመመለስ እንድትመኝ ሊያደርግህ ይችላል። ወደ ኋላ ግን አትመለስ። እንዲህ ዓይነቱ ጊዜ ሲደርስ በሕይወትህ አዲስና አስደናቂ የሆነ በረከት የምታገኝበት ደረጃ ላይ ልትሆን ትችላለህ። ይህ ደረጃ ጥልቅ የደስታ ስሜት የሚሰጥ ወደ ብስለት የሚመራ አዲስ እርምጃ ይሆናል። ምንም እንኳ ሰይጣን የስሜት ግለትህን በመጨመር ሊያስትህ ቢሞክርም የሰማይ አባትህ ሁሉን ቻይ የሆነ አምላክ የስሜት ግለትህን በማቀዝቀዝ ይቆጣጠርልሃል።

በአካል መብሰል እንኳ ሁልጊዜ ቀላልና የሚያስደስት ልምምድ አይደለም። ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት የሚተላለፍ ጎረምሳ የራሱ የሆነ ብስጭትና ውድቀት አለው። ይህም ሆኖ ያለማቋረጥ ዕድገቱን ከቀጠለ በመጨረሻው ወደ አስደናቂ የሕይወት ብስለት ይደርሳል። የክርስትና ዕድገት ልክ እንደ አካል ዕድገት በአንድ ጊዜ የሚሆን አይደለም። የክርስትና ብስለት ያለማቋረጥ ልንተጋበት የሚገባ ነገር ነው። ስለዚህ ተስፋ አትቁረጥ። በመውለድ ምጥ አለ፤ ደግሞም ወደ ብስለት በማደግም ውስጥ ምጥ አለ (ገላትያ 4፡19)።

በመጨረሻ መንፈሳዊ ዕድገታችንን መለካት ያለብን በእግዚአብሔር ቃል ነው። እራሳችንን መመዘን ያለብን በሌሎች ክርስቲያኖች ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር ልጅ ነው (ኤፌ. 4፡13)። በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ሕይወትህን እንድትመዝንባቸው በያዕቆብ መልእክት ላይ የተመሠረቱ በርካታ ጥያቄዎች አሉልህ። በየትኛውም ጊዜ ለመመልከት ነፃነት ይሰማህ። ምክንያቱም በየጊዜው የራስህን ሕይወት መመርመር ለመንፈሳዊ ጤንነት በጣም ጥሩ ነው።

በዕድሜ እየጨመረ የሚሄድ ሰው ሁሉ ያድጋል ማለት አይደለም። በዕድሜና በብስለት መካከል ልዩነት አለ። አንድ ክርስቲያን ደኅንነትን ካገኘ 10 ወይም 20 ዓመት መሆኑ ለመብሰሉ ዋስትና አይደለም። የበሰሉ ክርስቲያኖች ደስተኛ፥ ጠቃሚ፥ ሌሎችን ለመምከርና ለማበረታታት እንዲሁም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመገንባት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው። ያዕቆብን በጋራ ባጠናን ቁጥር በእግዚአብሔር እርዳታ በአንድነት እየተማርንና በአንድነት እየበሰልን እንሄዳለን።

ያዕቆብ 1:2-12

«ወንድሞቼ ሆይ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቊጠሩት። ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ሙሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።

«ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል። ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና። ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው።

«የተዋረደው ወንድም ግን በከፍታው ባለጠጋም በውርደቱ ይመካ፤ እንደ ሣር አበባ ያልፋልና። ፀሐይ ከትኩሳቱ ጋር ይመጣልና፥ ሣርንም ያጠወልጋልና፥ አበባውም ይረግፋልና፥ መልካም ውበት ይጠፋልና፤ እንዲሁ ደግሞ ባለጠጋው በመንገድ ይዝላል።

«በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸው የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።»

መከራን ወደ ድል መለወጥ

እንዲህ የሚል የእንግሊዝኛ አነጋገር አለ፡- «ሕይወት ሎሚን ሲያበረክትልህ ወደ ሎሚ ጭማቂ ለውጠው።» አባባሉን ሥራ ላይ ከማዋል ስቆ ማለፉ ይቀላል። የአባባሉ መሠረታዊ ፍልስፍና ግን ጥልቅና መሠረታዊ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባልም ነው። በመላው መጽሐፍ ቅዱሳችን ጥቃትን በድል፥ ፈተናን በአሸናፊነት የተወጡ ሰዎችን እንመለከታለን። ጥቃት የሚደርስባቸው ተሸናፊ ሰዎች ከመሆን ይልቅ ድል ነሺ ሆነዋል።

ያዕቆብ የሚናገረን ዛሬም ቢሆን ይህንኑ ልምምድ ልንለማመድ እንደምንችል ነው። ችግራችን ከውጭ የመጣ መከራም (1፡1-12) ይሁን ወይም ከውስጥ የሚነሣ ፈተና (1፡13-27) በክርስቶስ ባለን እምነት ድልን ልንለማመድ እንችላለን። የድል ውጤት መንፈሳዊ ብስለት ነው።

መከራን ድል መንሣት ከፈለግን አራት ትእዛዛትን መጠበቅ አለብን። እነዚህም፡- ቁጠር (1፡2)፤ እወቅ (1፡3)፤ ተው (1፡4፥ 9-11) እና ጠይቅ ወይም ፈልግ (1፡5-8) የሚሉ ናቸው። በሌላ መንገድ ለማስቀመጥ በመከራ ድል ለመንሣት የሚፈልጉ አራት ነገሮች ደስተኛ ዝንባሌ፥ የሚረዳ አዕምሮ፥ የሚገራ (የተገዛ) ፈቃድና ለማመን የሚፈልግ ልብ ናቸው።

መቁጠር፡- ደስተኛ ዝንባሌ (1፡2)

አመለካከት ውጤትን ዝንባሌ ደግሞ ተግባርን ይወስናል። እግዚአብሔር ፈተና እንደሚመጣ መጠበቅ እንዳለብን ነግሮናል። ይህ ቃል የሚለው «ልዩ ልዩ ፈተናዎች ቢደርስባችሁ» ሳይሆን «ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ» ነው። የክርስትና ሕይወት እጅግ ቀላል እንዲሆን የሚጠብቅ አማኝ አንዳንድ ጊዜ እጅግ አስደንጋጭ የሆነ ነገር ውስጥ እራሱን ሊያገኝ ይችላል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ» (ዮሐንስ 16፡33) በማለት አስጠንቅቋቸዋል። ጳውሎስ ወደ ክርስትና ላመጣቸው ሰዎች «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» (የሐዋ. 14፡22) በማለት ነግሮአቸዋል።

መከራ መቀበል ያለብን በእግዚአብሔር «ተበትነን ያለን ሕዝቦቹ» እንጂ በእግዚአብሔር «ተጠልለን ያለን ሕዝቦቹ» ስላልሆንን ነው። ሁልጊዜ ነገሮች ሁሉ እኛ በምንፈልገው መንገድ እንዲሄዱ መጠበቅ የለብንም። አንዳንድ መከራዎች ወደ ሕይወታችን የሚመጡት እንደግንኛውም ሰው ስለሆንን ነው። ለምሳሌ በሽታ፥ አደጋ፥ ተስፋ መቁረጥና አንዳንድ አሰቃቂ የሚመስሉ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ሌሎች መከራዎች ደግሞ ወደ ሕይወታችን የሚመጡት ክርስቲያኖች ስለሆንን ነው። ጴጥሮስ በመጀመሪያ መልእክቱ ስለ እንደዚህ ዓይነት መከራ ጽፏል፦ «ወዳጆች ሆይ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደመጣባችሁ አትደነቁ» (1ኛ ጴጥ. 4፡12) ሰይጣን ይዋጋናል፤ ዓለምም ትቃወመናለች ይህም ሕይወትን ጦርነት ያደርገዋል።

«መውደቅ» የሚለው ቃል በአጋጣሚ ስለ ደረሰ አደጋ የሚናገር አይደለም። «መጋፈጥ፥ ወይም መጋጠም» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። በእርግጥ ክርስቲያኖች መከራን አይፈጥሩም። «ልዩ ልዩ» ተብሎ በአማርኛ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል ትርጉም «በርካታ የተለያዩ ቀለማት ያሉት» ማለት ነው። 1ኛ ጴጥሮስ 1፡6 ላይ ጴጥሮስ ይህንኑ ቃል ተጠቅሞበታል። «... ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል» የሕይወት ፈተናዎች ሁሉ አንድ ዓይነት አይደሉም። አንድ የእጅ ጥበብ አዋቂ የሆነ ሰው እጅግ ውብ የሆነ ምንጣፍ ለመሥራት እንደሚጠቀምባቸው የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ክሮች ዓይነት ናቸው። እግዚአብሔር የሕይወትን ቀለማትና ልምምድ ሥርዓት ባለው መንገድ አቀናጅቶ በማስተካከል ያስቀምጣቸዋል። የመጨረሻው ውጤት ለክብሩ የሚሆን እጅግ ውብ ነገር ነው።

በአንድ ወቅት እኔና ባለቤቴ አንድ በዓለም ላይ የታወቀ ሽማኔ ጎበኘን። በድርጅቱ ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ወንዶችና ሴቶች በሽመና መሣሪያቸው ላይ ሆነው ሲሠሩ እናይ ነበር። ከሥር ያሉትን ክሮች በምንመለከታቸው ጊዜ የማያስደስቱ እንደነበሩ አስተዋልኩ። የተጠላለፉበት መንገድ በቀላሉ ለማየት የማይቻል ነበር። በሚገባ ያልተወጠሩ ክሮች ጫፋቸው የተወሳሰበ ነበር። ሥራውን ያስጎበኘን የነበረው ሰው እንዲህ አለ፦ «ሠራተኞቼንና ሥራውን ከተሳሳተ አቅጣጫ በመመልከት አትፍረዱ» ልክ እንደዚሁ እኛም ብዙ ጊዜ ሕይወትን ከተሳሳተ አቅጣጫ እንመለከተዋለን። ሕይወት መጨረሻው ምን እንደሚመስል የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህ

በእግዚአብሔርም ሆነ በሥራው ዛሬ በምናየው ነገር ላይ ብቻ ተመሥርተን አንፍረድ። ሥራው ገና አላለቀምና!

መሪ ቃሉ ቁጠር የሚል ነው። ይህ የሒሳብ ቃል ሲሆን ትርጉሙም «መመዘን» እንደ ማለት ነው። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 3 ውስጥ ይኸንን ቃል በርካታ ጊዜ ተጠቅሞበታል። ጳውሎስ ክርስቲያን በሆነበት ጊዜ ሕይወቱን በመመዘን ለሕይወቱ አዲስ ግቦችንና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች አበጀ። ከዚህ ቀደም እጅግ ጠቃሚ የነበሩ ነገሮች ከክርስቶስ ጋር ባለው የብርሃን ልምምድ ሲመለከታቸው «እንደ ምናምንቴ» ሆኑ። በሕይወታችን ፈተና በሚያጋጥመን ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ ባደረገው ነገር ብርሃንነት ልንመለከታቸው ይገባል።

ይኸ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወት ያለው ክርስቲያን በፈተና ውስጥ ሆኖ በእግዚአብሔር ደስ የሚሰኘው ለምን እንደሆነ ያስረዳናል። ከሁሉም የተሻለ ለሆነው ነገር ስለሚኖር ነው። ጌታ ኢየሱስም ቢሆን የመስቀልን ሞት የሚያህል መከራ የታገሠው «በፊቱ ስላለው ደስታ» ነው (ዕብ. 12፡2)። ይህም ደስታ ወደ ሰማይ በመመለስ ክብሩን ከቤተ ክርስቲያን ጋር መካፈሉ ነው።

ከመልካም ጸባይ ይልቅ ለምቾት አብልጠን ዋጋ የምንሰጥ ከሆነ ፈተና ይመጣና ተስፋ የሚያስቆርጠን ይሆናል። ከመንፈሳዊ ነገሮችም ይልቅ ለቁሳዊና ምድራዊ ነገሮች የበለጠ ዋጋም የምንሰጥ ከሆነ ትርፉ ጎዝጎዝ እንጂ ደስታ አይሆንም። የወደፊቱን ነገር እየረሳን ለዛሬ ብቻ የምንኖር ከሆነ ፈተናዎች የተሻልን ከማድረግ ይልቅ የበለጠ መራራ ያደርጉናል። ኢዮብ «የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ» (ኢዮብ 23፡10) በሚልበት ጊዜ የነበረውን ትክክለኛ አመለካከት እናያለን።

ስለዚህ መከራ በሚያጋጥምህ ጊዜ ወዲያውኑ ለጌታ ምስጋናን በማቅረብ የደስተኝነትን ዝንባሌ አዳብር። አታስመስል፤ እራስህንም ለማታለል አትሞክር። ዝም ብለህ ግን መከራዎችህን በእምነት ዓይን ተመልከታቸው። አመለካከት ውጤትን ይወስናል። በደስታ ለመፈጸም በደስታ ጀምር።

ግን በፈተና ውስጥ ሆኖ ደስ መሰኘት ይቻላልን? ሁለተኛው ትእዛዝ ይህንን የሚገልጥ ወይም የሚያስረዳ ነው።

እወቅ፡- አስተዋይ አዕምሮ (1፡3)

ፈተና በቀላሉ እንዲያልፉ ከፈተናውም እንዲጠቀሙ ክርስቲያኖች ምን የሚያውቁት ነገር አለ?

1. እምነት ሁልጊዜ ይፈተናል፡- እግዚአብሔር አብርሃምን በእምነት ይኖር ዘንድ ከጠራው በኋላ እምነቱን ለመጨመር ፈተነው። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚፈትነን ከፈተናው ውስጥ መልካምን ነገር ለማውጣት ሲሆን ሰይጣን ግን የሚፈትነን በፈተናው አማካይነት ክፉ ነገርን ለማምጣት ነው። በእምነታችን መፈተን በእውነት ዳግም መወለዳችንን ያረጋግጥልናል።

2. ፈተና ለእኛ መልካም ነገርን የሚያመጣ እንጂ የሚጎዳን አይደለም። ፈተና የሚለው ቃል «ማረጋገጫ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ይህን አሳብ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት የጴጥሮስን መልእክት መመልከት ይጠቅማል። «... በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ ...» (1ኛ ጴጥ. 1፡7) በማለት ወደሚፈተንበት ስፍራ ይመለከታል። የወርቅ ማዕድን ፈላጊ ወደ ናሙና ፈታኝ ዘንድ ያገኘውን ማዕድን ናሙና ይዞ ይመጣል። ወርቅ ይሁን አይሁን እንዲረጋገጥ ያመጣው ናሙና ዋጋ ከጥቂት ብሮች በላይ የማያወጣ ሊሆን ይችላል። ስለዚያ ናሙና የሚሰጠው ማረጋገጫ ዋጋ ግን በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ዋጋ ያለው ነው። ምክንያቱም ለማዕድን ፈላጊው የወርቅ ማዕድን መሬት እንዳለው ማረጋገጫ ነው። እግዚአብሔር ለእምነታችን የሚሰጠው ማረጋገጫ እጅግ የተከበረ ነው፤ ምክንያቱም እምነታችን እውነተኛ የመሆኑ ታላቅ ማረጋገጫ ነውና።

ፈተና ለአማኝ ጥቅሙ እንጂ ጉዳቱ አይደለም! ጳውሎስ እንዳለው «ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» (ሮሜ 8፡28)። ደግሞም «... ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና» (2ኛ ቆሮ. 4፡17)።

3. ፈተናን በትክክለኛ መንገድ ከተጠቀምንበት ለመንፈሳዊ ብስለት የሚረዳን ነው። እግዚአብሔር በሕይወታችን እንድናፈራው የሚፈልገው ነገር ምንድን ነው? ትዕግሥትን፥ ተስፋ ያለመቁረጥንና ነገሮች እጅግ ከባድ በሚሆኑበት ሰዓት እንኳ በዓላማ መጽናት ናቸው። «... መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ ትዕግሥትም ፈተናን፥ ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን በመከራችን ደግሞ እንመካለን» (ሮሜ 5፡3-4)

በመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ትዕግሥት ማለት ልናስወግዳቸው ስላልቻልን ብቻ ሁኔታዎችን በቸልተኝነት ስሜት መቀበል ማለት አይደለም። ትዕግሥት ማለት በመከራና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በርትቶና ጠንክሮ በዓላማ መቆም ማለት ነው።

ያልበሰሉ ሰዎች ሁልጊዜ ትዕግሥት የለሾች ናቸው። የበሰሉ ሰዎች ግን ትዕግሥተኛና ፅኑ ናቸው። ትዕግሥት የለሽነትና ያለማመን እንደ እምነትና ትዕግሥት ሁልጊዜ በአንድነት የሚሄዱ ናቸው። «በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ ...» (ዕብ. 6፡12)። «የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋል» (ዕብ. 10፡36)። «... የሚያምንም አያፍርም» (ኢሳይያስ 28፡16)።

እግዚአብሔር ታጋሾች ሊያደርገን ይፈልጋል። ምክንያቱም ለሌሎች በረከቶች ሁሉ ቁልፍ ትዕግሥት ስለሆነ ነው። ትዕግሥትን መማር የማይችል ትንሽ ልጅ ሌሎች ነገሮችን ለመማር አይችልም። አንድ አማኝ እግዚአብሔርን መጠበቅ ሲማር እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን ሊያደርግለት ይችላል። አብርሃም ከእግዚአብሔር ፊት ሮጦ አጋርን አገባ። በዚህም እርምጃው ወደ ቤተሰቡ ታላቅ ኃዘንን አመጣ። (ዘፍ. 16) ሙሴ እግዚአብሔርን ቀደመውና አንድ ሰው ገደለ። በዚህም ምክንያት ትዕግሥትን ይማር ዘንድ ለ40 ዓመታት በጎችን በመጠበቅ በምድረ በዳ አሳለፈ (ዘጸ. 2፡11-25) ጴጥሮስ እራሱ ትዕግሥት አጥቶ ሰው ሊገድል ምንም አልቀረውም ነበር (ዮሐ. 18፡10-11)።

እግዚአብሔር በሕይወታችን ትዕግሥትንና ሌሎች መሰል ባሕርያትን እንድናፈራ የሚያደርግበት ብቸኛ መንገድ ፈተና ነው። ትዕግሥት መጽሐፍ በማንበብ (ይህንን መጽሐፍ በማንበብ ቢሆንም እንኳ)፤ መልእክት በመስማትና በመጸለይ እንኳ ሊገኝ አይችልም። በሕይወት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ልናልፍ፥ በእግዚአብሔር ልንታመንና ለእርሱም ልንታዘዝ ይገባናል። ውጤቱ ትዕግሥትና ሌሎች መሰል ባሕርያትን በሕይወት ማሳደግ ይሆናል። ይህንን በማወቅ በፈተና ውስጥ በደስታ ማለፍ እንችላለን። ፈተና በሕይወታችን ምን እንደሚያደርግ፥ ለሕይወታችንም ምን ጥቅም እንደሚሰጥ እናውቃለን። የመጨረሻ ውጤቱ ደግሞ እግዚአብሔርን ማስከበር እንደሆነ እናውቃለን።

ይህ እውነታ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት በትዕግሥት ለማደግ እንዴት እንደሚጠቅም ይገልጽልናል (ሮሜ 15፡4)። ስለ አብርሃም፥

ስለ ዮሴፍ፥ ስለ ሙሴ፥ ስለ ዳዊትና ስለ ጌታም እንኳ ስናስብ እግዚአብሔር በፈተናዎች ውስጥ ዓላማ እንዳለውና በእርሱ ስንታመን ዓላማዎቹን እንደሚፈጽም እንገነዘባለን። አስተዋይ አእምሮን ሊተካ የሚችል ምንም ነገር የለም። ሰይጣን ቸልተኛ ክርስቲያንን ሊያሸንፍ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስን የሚያውቅና የእግዚአብሔርን ዓላማዎች የሚረዳ ክርስቲያንን ግን ሊያሸንፍ አይችልም።

መተው፡- ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገዛ የሰው ፈቃድ

(1:4፥ 9-11)

እግዚአብሔር ያለ እኛ ትብብር ባሕርያችንን ሊቀርጽ አይችልም። ልንተባበረው ፈቃደኛ ካልሆንን ፈቃዳችንን ለመግራት ይቀጣናል። ፈቃዳችንን ለፈቃዱ ካስገዛን ግን ሥራውን ይፈጽማል። እግዚአብሔር ተጀምሮ ወደ ፍጻሜ በማይደርስ ሥራ ደስተኛ አይደለም። እግዚአብሔር የተሟላና ፍጹም የሆነ ሥራን ይፈልጋል፤ የበሰለና ምሉዕ የሆነ ውጤትን ይፈልጋል።

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ሕይወት ያለው ዓላማ መንፈሳዊ ብስለት ነው። በቤታችን የሚወለዱ ሕፃናት ባያድጉና ሁልጊዜ ሕፃናት ቢሆኑ አስደንጋጭ ነገር ይሆን ነበር። ዕድገት ደስታን ብቻ ሳይሆን የራሱ ችግር ቢኖረውም ልጆቻችን እያደጉና እየበሰሉ መሄዳቸውን ማየት ያስደስተናል። ብዙ ክርስቲያኖች እራሳቸውን ከሕይወት ፈተናዎች ይከልላሉ፤ ስለዚህም ዕድገት አይታይባቸውም። እግዚአብሔር «ትናንሽ ልጆች» ወደ «ወጣትነት» እንዲያድጉ ወጣቶች ደግሞ «አባቶች» እንዲሆኑ ይፈልጋል (1ኛ ዮሐ. 2:12-14)።

ጳውሎስ በተሟላ ክርስትና ሕይወት ውስጥ የሚካተቱ ሦስት ተግባራትን ይጠቅሳል (ኤፌ. 2:8-10)። የመጀመሪያው፥ እግዚአብሔር ለእኛ የሚሠራው የደኅንነት ሥራ ነው። ይህንን ሥራ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ፈጽሞታል። በእርሱ ካመንን እርሱ ያድነናል። ሁለተኛው፥ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ የሚሠራው ሥራ ነው። «እኛ የእጁ ሥራ ውጤቶች ነንና።» ይህ ሥራ ቅድስና በመባል ይታወቃል። እግዚአብሔር ባሕርያችንን እየገነባ ሲሄድ የበለጠ ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰልን እንሄዳለን። «የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና» (ሮሜ 8:29)። ሦስተኛው ሥራ እግዚአብሔር በእኛ አማካይነት የሚሠራው ሥራ ነው። ይኸውም

አገልግሎታችን ነው። «በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርነው መልካሙን ሥራ ለማድረግ ነው።»

እግዚአብሔር እኛን ወደ አገልግሎቱ ከመጥራቱ በፊት በባሕርይ ይገነባናል። በእኛ አማካይነት ከመሥራቱ በፊት እኛን መሥራት አለበት። እግዚአብሔር ለአብርሃም የተስፋ ልጅ ከመስጠቱ በፊት ለ25 ዓመታት በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ሠርቶአል። እግዚአብሔር ዮሴፍን በግብፅ የጠቅላይ ሚንስትርነት ወንበር ላይ ከማስቀመጡ በፊት «በልዩ ልዩ ፈተናዎች» በማሳለፍ ለ13 ዓመታት በሕይወቱ ውስጥ ሠርቷል። ሙሴን ለ40 ዓመታት አገልግሎት ያዘጋጀው ዘንድ የወሰደው ጊዜ 80 ዓመታት ነው። ጌታ ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን ሕይወት ለማዘጋጀት ለሦስት ዓመታት አሠልጥኖአቸዋል።

ሆኖም እግዚአብሔር ያለፈቃዳችንና ያለ ስምምነታችን ሊሠራ አይችልም። ለእርሱ ፈቃድ የሚገዛ ፈቃድ ሊኖረን ይገባል። በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ሰው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አይከራከርም። በዚህ ፈንታ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በፈቃደኝነት ይቀበላል፤ በደስታም ይታዘዘዋል። «የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ» (ኤፌ. 6፡6)። ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በማያስገዛ መንፈስ በፈተና ውስጥ ለማለፍ ብንምክር ፍጻሜያችን እንደበሰለ አዋቂ ሰው ሳይሆን እንዳልበሰሉ ልጆች ይሆናል።

የዮናስ ሕይወት ለዚህ እውነት ጥሩ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር ዮናስን በነነዌ ለሚገኙ አሕዛብ እንዲሰብክ አዘዘው፤ ዮናስ ግን እምቢ አለ። ይህ ነቢይ ተልእኮውን እንዲፈጽም እግዚአብሔር ቀጣው። ከቅጣቱም በኋላ እንኳ ዮናስ እግዚአብሔርን የታዘዘው ከልቡ አልነበረም። ቅጣት ቢቀምስም አላደገም፤ ይህንን የምንረዳው በመጨረሻው ምዕራፍ በተጻፈው ታሪክ ነቢዩ ልክ እንደ አንድ የማይረባ ሕፃን ዓይነት ባሕርይ ስለምናይበት ነው። ከከተማይቱ ውጭ ተቀምጦ እንደከፋው ሕፃን በማኩረፍ እግዚአብሔር በዚያች ከተማ የሚያመጣውን ፍርድ ይጠባበቅ ነበር። በፀሐዩ፥ በነፋሱ፥ በቅሊቱ፥ በትሉና በእግዚአብሔር ይበሳጭ ነበር።

የብስለት አንዱ ከበድ ያለው ወይም አስቸጋሪው እርምጃ ከለመድነው ነገር መላቀቅ ነው። ይህ ከልማድ መላቀቅ አንድ ሕፃንን ጡት ከማስጣል ጋር ሊወዳደር ይችላል። በዚህ እርምጃ ሕፃኑ የእናቱ ፍቅር እንደተቋረጠበት፥ ነገሮች ሁሉ የእርሱ ተቃራኒ እንደሆኑ ያስብ

ይሆናል። ይህ እርምጃ ግን በትክክለኛው መንገድ ከታየ የብስለትና የነፃነት እርምጃ ነው። ለሕፃኑ በጣም መልካም የሆነ እርምጃ ነው። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ልጆቹ ከልጅነት የመጫወቻ ዕቃቸውና እንጭጭ ከሆነ ወይም ካልበሰለ ዝንባሌያቸው እንዲላቀቁ ይፈልጋል። ይህንን ተግባራዊ ምሳሌ ዳዊት በመዝሙር 131 ላይ ሲጠቀምበት እንመለከታለን። «ነፍሴን አሳረፍኋት፤ የእናቱንም ጡት እንዳስተዉት ዝም አሰኘኋት፤ ነፍሴ የእናቱን ጡት እንዳስተዉት በእኔ ውስጥ ናት» (ቁ. 2)። ከልጅነት ባሕርያችን ለማላቀቅ እግዚአብሔር በፈተናዎች ይጠቀማል። ፈቃዳችንን ለፈቃዱ ካላስገዛን ግን የበለጠ እንጭጭና ያልበሰልን እንሆናለን።

ከቁጥር 9-11 ያዕቆብ ይህንን መመሪያ ከሁለት ዓይነት ክርስቲያኖች ጋር ያዛምደዋል። እነዚህን ሁለት ዓይነት ክርስቲያኖች የተዋረደና ባለ ጠጋ በማለት ይጠራቸዋል። በዚህ መልእክት ውስጥ በግልጽ እንደምናየው ገንዘብና የኅብረተሰቡ የኑሮ ደረጃ በመካከላቸው ግልጽ ችግር ሆኖ ነበር፤ (2፡1-7ን ከ15-16 ጋር፤ 4፡1-3ን ከ13-17 እና 5፡1-8 ጋር ተመልከት)። የእግዚአብሔር መመዘኛዎች ግን ሁሉን የሚያስተካክሉበት መንገድ አላቸው። አንድ ፈተና ወደ አንድ ደህ ሰው ሲመጣ እግዚአብሔር የወደደውን ነገር እንዲያደርግ በመፍቀድ ከእርሱ ሊወሰድ የማይቻለውን መንፈሳዊ ብልጽግና በማግኘቱ ደስ ሊሰኝ ይገባዋል። አንድ ፈተና ወደ ባለጠጋ ሰው በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ እርሱም ቢሆን እግዚአብሔር የወደደውን ነገር እንዲያደርግ በመፍቀድ በክርስቶስ ያለው ብልጽግና ደግሞ ሊጠወልግና ሊበላሽ እንደማይችል በማሰብ ደስ ሊሰኝ ይገባዋል። በሌላ አባባል በሕይወት ፈተናዎች ውስጥ ሊያሳልፍ የሚቻለው ቁሳዊ ብልጽግናህ ሳይሆን መንፈሳዊ ብልጽግና ነ ው ማለት ነው።

እስካሁን ድረስ ከያዕቆብ መልእክት ሦስት ትእዛዛትን ተመልክተናል። እነዚህንም ቁጠር፡- የደስተኛነት ዝንባሌ፥ እወቅ፡- አስተዋይ ወይም የሚገነዘብ አእምሮ፥ ተው፡- ለእግዚአብሔር እራስን የሚያስገዛ ፈቃድ ናቸው። ያዕቆብ አራተኛ ትእዛዝ ደግሞ ይሰጣል።

ጠይቅ፡- የሚያምን ልብ (1፡5-8)

ያዕቆብ ይህንን መልእክት የሚጽፍላቸው ሰዎች በጸሎት ሕይወታቸው ችግር ነበረባቸው (4፡1-3፤ 5፡13-18)። እግዚአብሔር ፈቅዶ ወደ ሕይወታችን በሚመጡ ችግሮች ውስጥ

ስናልፍ ምን ብለን መጸለይ አለብን? ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጥበብን ጠይቁ፥ የሚል መልስ ይሰጠናል።

ያዕቆብ ስለ ጥበብ የሚናገረው በርካታ ነገር አለው (1፡5፤ 3፡13-18)። መጽሐፈ ምሳሌ እንደሚያረጋግጥልን የአይሁድ ሕዝብ ጥበብን አፍቃሪዎች ነበሩ። አንድ ሰው እንዲህ አለ፡- እውቀት ነገሮችን በተናጠል የመገንዘብ ችሎታ ሲሆን ጥበብ ግን በተናጠል የተገነዘብናቸውን ነገሮች በአንድነት የማቀናበር ችሎታ ነው። ጥበብ እውቀትን በትክክለኛ መንገድ ለመጠቀም መቻል ነው። ሁላችንም ብንሆን የተማሩ ሞኝ ሰዎችን እናውቃለን። እነዚህ ሰዎች በቀለም ትምህርት ችሎታቸው እጅግ አስደናቂ ውጤት ቢኖራቸውም በሕይወታቸው ግን እጅግ ቀላል የሆነውን ውሳኔ እንኳ መወሰን አይችሉም። አንድ ጊዜ በአንድ ሴሚናሪ ውስጥ ከፍተኛ ችሎታ ያለው አንድ ፕሮፌሰር ሁለት ኮፊያዎች አድርጎ አየሁት።

በፈተና ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ ጥበብ የሚያስፈልገን ለምንድን ነው? ብርታትን ወይም ጸጋን ወይም ከፈተናው ነፃ መውጣትን እንኳ የማንጠይቀው ለምንድን ነው? ጥበብን መጠየቅ ያለብን እግዚአብሔር በዚህ ውስጥ መንፈሳዊ ብስለት እንድናገኝ ያዘጋጀው ዕድል እንዳያመልጠን ነው። ጥበብ እነዚህን ሁኔታዎች ለጥቅማችንና ለእግዚአብሔር ክብር እንዴት እንደምናውለው እንድንረዳ ይጠቅመናል።

አብራኝ የምትሠራ ጸሐፊ እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ፈተናዎች እያለፈች ነበር። እርሷ በድንገት የሚነሣ ሕመም ነበረባት። ባለቤቷ ዕውር ሆነና እንደሚሞት እርግጠኛ ወደሆነበት ሆስፒታል ተወስዶ ነበር። አንድ አሑድ ቤተ ክርስቲያን ተገናኘንና እንደምጸልይላት ነገርኳት።

«ለመሆኑ ስትጸልይ እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግልኝ ነው የምትጠይቀው?» ብላ ጠየቀችኝ። ጥያቄዋ አስደነቀኝና እግዚአብሔር እንዲረዳሽና ብርታቱን እንዲሰጥሽ ነው የምጸልይልሽ አልኳት። እርሷም መልሳ «ስለ ጸሎትህ አመሰግንሃለሁ፤ ነገር ግን ስለ አንድ ተጨማሪ ነገር ጸልይልኝ። ይኸውም ከእነዚህ ነገሮች የሚገኘውን መልካም ነገር ሁሉ እንዳላጣ እግዚአብሔር ጥበብን እንዲሰጠኝ ጸልይልኝ» አለችኝ። ይህች ሴት የያዕቆብ 1፡5ን ትርጉም በሚገባ ተረድታ ነበር።

ያዕቆብ የሚነግረን ጥበብን መጠየቅ እንዳለብን ብቻ ሳይሆን እንዴት መጠየቅ እንዳለብንም ነው። መጠየቅ ያለብን በእምነት ነው። እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሊመልስ ስለሚፈልግ ልንፈራ አይገባም።

እግዚአብሔር በእኛ ላይ ለመቆጣት ስሕተትን የሚፈልግ አይደለም። «ለትሑታን ጸጋን ይሰጣል» (ያዕቆብ 4፡6) ጥበብን ይጨምርልናል። አለማመን ጸሎታችን መልስ እንዳያገኝ አደገኛ ዕንቅፋት ነው።

ያዕቆብ ተጠራጣሪ ክርስቲያንን በማዕበል ከሚገላታ ባሕር ጋር ያወዳድረዋል። አንድ ጊዜ ከፍ፥ ከደቂቃ በኋላ ደግሞ ዝቅ ይላል። ሃዋይ በተባለች ደሴት ዕረፍት ላይ በነበርኩበት ጊዜ ማዕበልን መተማመን እንደማይቻል ተማርኩ። በባሕሩ አጠገብ ባለ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብዬ ማዕበሉን እየተመለከትኩ በፀሐይ ብርሃን ስደሰት ሳለሁ ከኋላዬ አንድ ድምፅ ሰማሁ። እየመጣ ያለው ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ዞር ስል ከባድ ማዕበል ይዞት በመጣው ውኃ ተጠመቅኩ። ጀርባችሁን ለማዕበል ምንም ቢሆን አትስጡ። ምክንያቱም አንድ ጊዜ ወደ ላይ አንድ ጊዜ ወደ ታች በማለት አደጋን ስለሚያስከትል የማይታመን ነው።

ሁለት አሳብ ያለው በመንገድም የሚያወላውል ሰው እንደዚሁ ነው። እምነት «ይቻላል» ወይም «አዎ» ሲል ያለማመን (ጥርጣሬ) ደግሞ «አይቻልም» ወይም «አይሆንም» ይላል። ስለዚህ ጥርጣሬ አንድ ጊዜ «ይቻላል» ይላል። ወዲያውኑ ደግሞ በደቂቃ ውስጥ «አይቻልም» ይላል። ጴጥሮስ በውኃ ላይ እየተራመደ ወደ ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ ሊሰምጥ የነበረው በመጠራጠሩ ነበር፤ (ማቴ. 14፡22-33)። በዚህ ምክንያት ነበር ኢየሱስ «አንተ እምነት የጎደለህ ስለምን ተጠራጠርህ?» ያለው። ጴጥሮስ የእምነት እርምጃውን በጀመረ ጊዜ ዓይኖቹን በክርስቶስ ላይ አድርጎ ነበር። ነፋሱና ማዕበሉ መረበሽ በጀመሩ ጊዜ ግን በእምነት መራመዱ አበቃና መስመጥ ጀመረ። በሁለት አሳብ በማመንታቱ ሙሉ በሙሉ ሊሰምጥ የቀረው በጣም ትንሽ ነበር።

ብዙ ክርስቲያኖች ማዕበል በሚያንገላታው ውኃ ላይ እንዳለ ኩበት ሆነው ይዋልላሉ። አንድ ጊዜ ከፍ ወዲያው በደቂቃ ውስጥ ደግሞ ዝቅ እያሉ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ይንገላታሉ። እንዲህ ዓይነቱ ኑሮ ያለመብሰል (የእንጭጭነት) ማስረጃ ነው። ጳውሎስ በኤፌሶን 4፡14 ላይ ተመሳሳይ አሳብ ይጠቀማል። «እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደፊት አይገባንም»። የሚያምንና አንድ አሳብ ያለው ልብ ካለን በእምነት ልንጠይቅ እንችላለን። እግዚአብሔርም የሚያስፈልገንን ጥበብ ይሰጠናል። ያለመረጋጋትና ያለመብሰል የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው።

ያዕቆብ ይህንን ክፍል የሚደመድመው በቃለ ቡራኬ ነው፡- «በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው» (ያዕቆብ 1፡12)። በቁጥር 2 ላይ በደስታ ይጀምራል ደግሞ በደስታ ይፈጽማል። በመጨረሻ የሚገኘው ውጤት የሚወሰነው በመነሻው ባለን አመለካከት ነው። ይህ ቡራኬ ከፍተኛ ማበረታቻ ነው። ምክንያቱም በትዕግሥት ፈተናን የሚቀበሉ ሰዎች አክሊል እንደሚጠብቃቸው ይናገራል። ጳውሎስ በመልእክቶቹ ውስጥ ሯጭን በምሳሌነት በተደጋጋሚ ያቀርበዋል። ያዕቆብም በዚህ ስፍራ የሚያደርገው ይህንኑ ነው። አንድ ኃጢአተኛ ደኅንነትን ያገኘው ፈተናን በትዕግሥት በመቀበል ነው አይልም፤ ነገር ግን አንድ አማኝ ፈተናን በትዕግሥት በመቀበሉ ሽልማትን ያገኛል ይላል።

ሽልማትን የሚያገኘው እንዴት ነው? በመጀመሪያ፥ ክርስቲያናዊ በሆኑ ባሕርያት በማደግ ነው። ይህ ከማንኛውም ነገር ሁሉ የላቀ ነው። በተጨማሪ፥ ሽልማቱን የሚያገኘው ለእግዚአብሔር ክብርን በማምጣትና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ የሕይወትን አክሊል በመቀበል ነው። በመጀመሪያ መስቀል፥ ቀጥሎ አክሊል፤ በመጀመሪያ መከራ ወይም ስቃይ ቀጥሎ ክብር። እግዚአብሔር የሚረዳን ፈተናዎችን በማስወገድ አይደለም፤ ነገር ግን በፈተናዎቹ ውስጥ የሚገኙትን መልካም ነገሮች እንዳያመልጡን በማድረግ ነው። ሰይጣን ፈተናዎቹን እኛን ለማጥፋት ሊጠቀምባቸው ይፈልጋል። እግዚአብሔር ግን እኛን ለመገንባት ይጠቀምባቸዋል።

ያዕቆብ በቁጥር 12 ላይ ለሚወዱት የተባለውን እጅግ በጣም ጠቃሚ ቃል ይጠቀማል። እግዚአብሔር ለሚታዘዙት ወይም ለሚታመኑበት ተስፋ የሰጠውን የሕይወትን አክሊል ጉዳይ እንዲጽፍ እናስብ ነበር። ታዲያ ያዕቆብ በዚያ ምትክ ለሚወዱት የሚለውን ቃል ለምን ተጠቀመ? ምክንያቱም መውደድ በዚህ ክፍል ውስጥ የተሰጡ ትእዛዞችን ሁሉ ለመጠበቅ የሚያነሣሣ መንፈሳዊ ኃይል ስለሆነ ነው።

በፈተና ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ የደስተኛነት ዝንባሌ ያለን ለምንድን ነው? ምክንያቱም እግዚአብሔርን ስለምንወደው ነው። እርሱም እኛን ስለሚወደንና ክፉ ነገርን ስለማያደርስብን ነው። እውነትን የሚያገናዝብና የሚረዳ አእምሮ ያለን ለምንድን ነው? ምክንያቱም እርሱ ስለሚወደንና እውነቱን ስላካፈለን በዚህም ምክንያት እኛም ስለምንወደው ነው። ፈቃዳችንን ለእርሱ የምናስገዛው ለምንድን ነው? ስለምንወደው ነው። ፍቅር ባለበት መገዛትና መታዘዝ አለ። የሚያምን ልብ ያለን ለምንድን ነው? ምክንያቱም ፍቅርና እምነት በአንድነት

የሚሄዱ ስለሆነ ነው። አንድን ሰው ስትወደውና ስታምነው እርዳታን ከመጠየቅ ወደ ኋላ አትልም።

ያዕቆብ ከሚሰጣቸው ትእዛዛት በስተጀርባ ያለው መንፈሳዊ ኃይል ፍቅር ነው። እግዚአብሔርን ከወደድነው ለመቁጠር፥ ለመረዳት፥ ለመተውና ለመጠየቅ አንቸገርም። በዚህ ነገር ውስጥ የሚካተት ሌላ ጉዳይም አለ። ፍቅር ለእግዚአብሔር ታማኝ እንድንሆን ያደርገናል። የሚያመነታ ሰው (1፡8) ታማኝ እንዳልሆነ ባል ወይም ታማኝ እንዳልሆነች ሚስት ነው። እግዚአብሔርንም ዓለምንም ለመውደድ ይፈልጋል። ያዕቆብ እንዲህ በማለት ይመክረናል፡- «ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ ልባችሁን አጥሩ» (ያዕቆብ 4፡8)። ልባችሁን አጥሩ የሚለውን ቃል የግሪክ ቀጥተኛ ትርጉም «ንጹሐን ሁኑ» ማለት ነው፤ የሚገልጸውም ታማኝ ስላልሆነ አፍቃሪ ነው።

ወደ ጡት ማስጣል መግለጫ እንመለስ። እናቱን የሚወድና እናቱም እርሱን እንደምትወደው እርግጠኛ የሆነ ሕፃን ጡት በመጣሉ ሂደት ውስጥ ሊያልፍና ማደግ ሊጀምር ይችላል። እግዚአብሔርን የሚወድና እግዚአብሔርም እንደሚወደው የሚያውቅ ክርስቲያን እግዚአብሔር ፈተና ወደ ሕይወቱ እንዲመጣ በሚፈቅድበት ጊዜ አይፍረከረክም። በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ ዋስትና ያለው ሰው ነው። እግዚአብሔርንም ዓለምንም ለመውደድ በመሞከር በሁለት አሳብ አያመነታም። ሎጥ በሁለት አሳብ የሚያመነታ ሰው ነበር። ስለዚህ ፈተና ወደ ሕይወቱ በመጣ ጊዜ ክፉ አወዳደቅን ወደቀ። አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር። እግዚአብሔርን የሚወድና በእርሱ የሚታመን ነበር። ፈተና ወደ ሕይወቱ በመጣ ጊዜ በድል ተወጣውና በእምነቱ የብስለትን ዕድገት ዐደገ።

እግዚአብሔር በመከራዎች ውስጥ ያለው ዓላማ ብስለት ነው። «ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ነገር ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም»። የቻርልስ ቢ ዊልያምስ ትርጉም በሥዕላዊ አቀራረብ እንዲህ ብሎ አስቀምጦታል፡- «ትዕግሥታችሁ ግን ወደ ፍጹምነት ደረጃ እንዲደርስና በዚህም በሚገባ እንድታድጉና በፍጹምነት ለሥራው የተዘጋጃችሁ እንድትሆኑ ...»

የምትፈልገው ይህንን ከሆነ ለክርስቶስ ካለህ ፍቅር የተነሣ ቁጠር፤ እወቅ፤ ተውና ጠይቅ።

ያዕቆብ 1፡13-18

«ማንም ሲፈተን በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና እርሱ ራሱ ማንም አይፈትንም። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።

«የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ አትሳቱ በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው። መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ። ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን።»

ፈተናን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል

በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ሰው በፈተና ውስጥ ታጋሽ ነው። ፈተናዎቹ አንዳንድ ጊዜ ከውጭ የሚመጡ ችግሮች ወይም መከራዎች ሲሆኑ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከውስጥ የሚነሡ ይሆናሉ። ፈተናዎች በእግዚአብሔር የሚላኩ ወይም በሰይጣንና በወደቀው ተፈጥሮአችን የሚደገፉ ሊሆኑ ይችላሉ። ያዕቆብ በዚህ ክፍል የሚናገረው ስለዚህ ስለ ሁለተኛው ዓይነት ግለትም ከውስጥ ስለሚነሣው የፈተና ዓይነት ነው።

ምናልባት እንዲህ ብለን ልንጠይቅ እንችል ይሆናል። «ያዕቆብ እነዚህን ሁለት ነገሮች በማገናኘት የተናገረው ለምንድነው? ከውጭ በሚነሡ ፈተናዎችና ከውስጥ በሚነሡ ግለትም በራስ አሳብና ምኞት በመታለል የሚመጡ ፈተናዎች መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?» በቀላሉ ነገሩ እንደዚህ ነው፦ ካልተጠነቀቅን በስተቀር በውጭ የሚመጡ ፈተናዎች በራስ አሳብና ምኞት የመታለያ ውስጣዊ ፈተናዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ልናጉረመርም እንችላለን። እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር መጠራጠር ስንጀምር ለፈቃዱ ለመገዛት እምቢተኞች ልንሆን እንችላለን። በዚህ ጊዜ ካለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የምናመልጥበትን ዕድል ሰይጣን ሊያዘጋጅልን ይችላል። ይህ ዕድል ራሱ ፈተና ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንን እውነት የሚያስረዱ በርካታ ምሳሌዎች አሉ። አብርሃም ወደ ከነዓን በደረሰ ጊዜ በዚያ ራብ እንዳለ ተመለከተ። የጋማና የቀንድ ከብቶቹንም በሕይወት ለማቆየት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማግኘት አልቻለም ነበር። ይህ መመዘኛ የእግዚአብሔርን ማንነት ለማረጋገጥ ጥሩ ዕድል ነበር። አብርሃም ግን ይህንን ዕድል ወደ ፈተና በመቀየር የራሱን እርምጃ ወሰደ፤ ወደ ግብፅ ወረደ። እግዚአብሔር አብርሃምን ወደ መታዘዝና ወደ በረከት እንደገና ያመጣው ዘንድ መቅጣት ነበረበት። እስራኤላውያን በምድረ በዳ ይንከራተቱ በነበረበት ወቅት ሕዝቡ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር እምነታቸው ለማየት ይልከው የነበረውን ሙከራ ወደ ፈተናዎች እየቀየሩ ጌታን ይፈታተኑ ነበር። ከግብፅ ነፃ ከወጡ በኋላ ብዙ ሳይቆዩ ውኃ ያገኙበት የነበረው መንገድ ተሟጥጦ አለቀና ያለ ውኃ ለሦስት ቀናት ተጓዙ። ከሦስት ቀናት በኋላ ያገኙትም ውኃ ሊጠጣ የማይቻል እጅግ

መራራ ነበር። ስለዚህ ወዲያውኑ ያጉረመርሙና እግዚአብሔርን ያማርሩ ጀመር። ወደ እነርሱ የመጣውን መመዘኛ ወደ ፈተና ቀየሩትና በፈተናው ወደቁ።

እግዚአብሔር በፈተና እንድንሸነፍ አይፈልግም፤ ይሁን እንጂ በፈተና ውስጥ ከማለፍ አያግደንም። እኛ ለእግዚአብሔር የተከለሉ ወይም ተለይተው የሚኖሩ ሕዝቦች ሳንሆን ለእግዚአብሔር የተበተኑ ሕዝቦች ነን። በመንፈሳዊ ሕይወት ወደ ብስለት ደረጃ ልንደርስ ካስፈለገ መከራዎችንንና ፈተናዎችን መቀበል አለብን። ፈተናን መቋቋም እንድንችል ልናስተውላቸው የግድ የሚያስፈልጉን ሦስት እውነታዎች አሉ።

የእግዚአብሔርን ፍርድ አስብ (1፡13-16)

ይህ አሉታዊ የሆነ አቀራረብ ቢሆንም እጅግ ጠቃሚ ነው። ያዕቆብ እንዲህ አለ «አሻግራችሁ የኃጢአት ፍጻሜ ምን እንደሆነ ተመልከቱ - ሞት ነው» በፈተና ጉዳይ ግንም ሰው እግዚአብሔርን ሊወቅስ አይገባም። ሊፈተን የማይችል ፍጹም ቅዱስ ነው። ሌሎችን እንዳይፈትን ደግሞ አፍቃሪ ነው። እግዚአብሔር በአብርሃም እንዳደረገው እምነታችንን ለማየት በሕይወታችን አንዳንድ ነገሮችን በማምጣት ይመዝነን ይሆናል (ዘፍ. 22)። ነገር ግን አይፈትነንም ሊፈትነንም አይችልም። እግዚአብሔር እምነታችንን ለማየት ወደ ሕይወታችን የሚያመጣቸውን መመዘኛዎች ወደ ፈተና የምንለውጠው ግን እኛው እራሳችን ነን።

ፈተና አንድ መልካም ነገርን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በሆነ መጥፎ መንገድ እንዲሳካ ለማድረግ በተገኘው ዕድል መጠቀም ማለት ነው። አንድን የትምህርት ፈተና ለማለፍ መፈለግ ስሕተት ነውን? ጨርሶ ስሕተት አይደለም። ነገር ግን ፈተናውን ለማለፍ ተብሎ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ማጭበርበር ኃጢአት ነው። በዚህ ሁኔታ የምናየው የማጭበርበር ፈተና አንድን መልካም ነገር በመጥፎ መንገድ ስኬታማ የማድረግን ዕድል መጠቀም ነው። ምግብ መብላት ስሕተት አይደለም፤ ነገር ግን ምግብ ለመብላት ብሎ መስረቅን ማሰብ እራስን መፈታተን ነው።

ስለ ኃጢአት ስናስብ አንድ ብቸኛ ተግባር ይመስለናል። እግዚአብሔር ግን ኃጢአትን እንደ ሂደት ይመለከተዋል። አዳም የፈጸመው ኃጢአት መተላለፍ ነበር። ይህ መተላለፍ ደግሞ ኃጢአትን÷

ሞትንና ፍርድን በሰው ልጆች ሁሉ ላይ አመጣ። ያዕቆብ ይህንን የኃጢአት ሂደት በአራት ደረጃዎች አስቀምጦታል።

ምኞት (1፡14)፡- ይህ ምኞት የሚለው ቃል የሚገልጠው ማንኛውንም ዓይነት ፍላጎት እንጂ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎትን ብቻ አይደለም። በሕይወት ውስጥ ጤነኛ የሆኑ ማናቸውም ዓይነት ፍላጎቶች ከእግዚአብሔር የተሰጡንና በራሳቸው ምንም ክፋት የሌለባቸው ናቸው። ያለ እነዚህ ፍላጎቶች ተግባራችንንም በትክክል ለማካሄድ አንችልም። የራብና የጥማት ስሜት የሚሰማን ባንሆን ኖሮ ልንበላም ሆነ ልንጠጣ አንችልም ነበር። በዚህም ምክንያት እንሞት ነበር። ድካም ባይኖር ኖሮ ሰውነታችንን ለማሳረፍ አንነሣሣም ነበር፥ ይህም እንድንዝልና ከጥቅም ውጭ መሆንን ያስከትል ነበር። የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ጤናማ ፍላጎት ነው። ያለዚህ ፍላጎት የሰው ልጅ ዘር ሊቀጥል አይችልም ነበር።

እነዚህን ፍላጎቶቻችንን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በሆነ መንገድ ለማርካት ስንሞክር ችግር ውስጥ እንገባለን። መብላት ትክክለኛና ጤናማ ነገር ነው። በስስታምነት መንፈስ ከዓቅም በላይ ግግበስበስ ግን ኃጢአት ነው። መተኛት ጤናማ ነገር ነው፤ ስንፍና ግን ኃጢአት ነው። «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል» (ዕብ. 13፡4)።

አንዳንድ ሰዎች እነዚህን ጤናማ ፍላጎቶች በመካድ ወይም በመጨቆን «መንፈሳዊ» ለመሆን ይጥራሉ። ይህ ነገር ግን ሰብአዊነታቸውን ከማሳነስ ሌላ ምንም አይጠቅማቸውም። እነዚህ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች እንደ አንድ መኪና ይመስላል። አንድ መኪና እንዲሽከረከር ከተፈለገ ነዳጅን መጨመር ያስፈልጋል። ነዳጁ(ቤንዚኑ) ካለቀ መኪናውን የሚያንቀሳቅሰው ኃይል አይኖርም። ነዳጁ በብዛት ከተለቀቀ ደግሞ አደጋ ይፈጠራል። ስለዚህ ምስጢሩ ካለማቋረጥ መቆጣጠር ነው። እንደዚሁም ፍላጎቶቻችንን በመቆጣጠር እነርሱ እኛን ከሚገዙን ይልቅ እኛ ገዥዎቻቸው ስለምንሆን እንደፈለግን ልናዝዛቸው እንችላለን። ይህንንም ልናደርግ የምንችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው።

መሳብና መታለል (1፡14)፡- ማንኛውም ፈተና ወደ ሰው የሚመጣው ፈተና መስሎ አይደለም። ሁልጊዜ ከእውነታው ይልቅ የሚስብና የሚያስደስት መስሎ ይቀርባል። ያዕቆብ ይህንን ነጥብ ለማረጋገጥ ከስፖርት ዓለም ሁለት ምሳሌዎችን ይጠቀማል። መሳብ

የሚለው ቃል አንድን ነገር ወደ ወጥመድ ለመክተት የማባበያ መንገድን የሚያመለክት ሲሆን መታለል በሚል የአማርኛ ቃል የተተረጎመው ቃል የግሪኩ ቃል አሳብ ደግሞ አታልሎ በመንጠቆ መያዝን የሚያመለክት ነው። በአደን ሥራ ላይ የተሠማራ ሰውም ሆነ ዓሣ አጥማጅ የፈለጉትን ነገር ለመያዝ መሳቢያ ምግብ በመንጠቆው ማቅረብ አለባቸው። ማንኛውም እንስሳ እያወቀ ወደ ተጠመደለት ወጥመድ አይገባም። ማንኛውም ዓሣ ደግሞ እያወቀ የመንጠቆውን ጫፍ አይነክስም። የመሳቢያው ምግብ ዓላማ መንጠቆውንና ወጥመድን ሰውሮ ከማቅረቡ ላይ ነው።

ፈተና ሁልጊዜ ተፈጥሮአዊ ፍላጎታችንን የሚያነሣሣ አንድ የማጥመጃ ወይም የመሳቢያ ነገር አለው። ይህ ማባበያ መልካም መስሎ ወደ ወጥመዱ እንድንገባ ከመሳብ ሌላ ትክክለኛውን እውነታ በመሸፈን በመጨረሻ ኃዘንንና ቅጣትን ያመጣብናል። እጅግ ደስ የሚያሰኝ መስሎ በመቅረብ ልብን የሚያዘናጋው ማባበያው ወይም ማጥመጃው ነው። ሎጥ «በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውንም ውኃ የሞላበትን ሀገር» ባያይ ኖሮ ወደ ሰዶም አይንቀሳቀስም ነበር (ዘፍ. 13፡10-18)። ዳዊት በቤቱ አጠገብ ይኖር የነበረውን ሰው ሚስት ሲመለከት እጅግ አሳዛኝ ውጤት እንደሚያስከትልበት ቢያስብ ኖሮ ከእርስዋ ጋር ባላመነዘረም ነበር። እጅግ አሳዛኝ ውጤቱም ከቤርሳቤህ የተወለደው ልጅ መሞት፤ ኦርዮን የተባለው ጠንካራ ወታደር መገደልና ትዕማር የተባለችውን ሴት ልጅ መደፈር ነበር። ማባበያው ወይም ማጥመጃው ኃጢአት የሚያስከትለውን ውጤት እንዳንመለከት ያደርጋል።

ኢየሱስ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ ለፈተናዎቹ ሁሉ መልስ የሰጠው ከእግዚአብሔር ቃል ነበር። ስለዚህም ሦስት ጊዜ «ተብሎ ተጽፏል» በማለት መልስ ሰጠ። በሰብአዊ አመለካከት ስናየው ድንጋዮችን ወደ ዳቦ በመለወጥ ራብን ማስታገስ በጣም ትክክለኛ ነገር ነው። ይህ ግን ከእግዚአብሔር አመለካከት አንፃር አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስህን በሚገባ ስታውቅ ማባበያውን ለመለየትና በወሳኝነት ፈተናውን ለመቋቋም ትችላለህ። በማየት ሳይሆን በእምነት መራመድ ማለት ይህ ነው።

ያለመታዘዝ (1፡15)፡- ከስሜታዊነት (ምኞት) በእውቀት ከሚገለጠው (መሳብ ወይም መታለል) አልፈን ወደ ፈቃድ ተሸጋግረናል። ያዕቆብ በአዳኝና በዓሣ ማጥመድ ምሳሌነት ሲገልጠው የቆየውን ነገር በመለወጥ አሁን ደግሞ በልጅ መውለድ ሂደት ውስጥ ያሉትን ነገሮች ምሳሌ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል። ምኞት የመሳቢያውን

ምግብ ለመውሰድ ዘዴን ትፀንሳለች። ፈቃድም ነገሩን ያረጋግጥና ይተባበራል ውጤቱም ኃጢአት ይሆናል። ይህ ሂደት ተሰማንም አልተሰማንም በመንጠቆው ተይዘን በመረቡ ተጠመድን ማለት ነው። ሕፃን ተወልዶአል እስኪጎረምስ መጠበቅ ብቻ ነው! የክርስትና ሕይወት የፈቃድ እንጂ የስሜት ጉዳይ አይደለም። ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች እንዲህ ሲሉ እሰማለሁ፡- «መጽሐፍ ቅዱስ እንዳነብ አልተሰማኝም፥ ወይም የጸሎት ስብሰባዎችን እንድካፈል አልተሰማኝም።» ልጆች በስሜታቸው መሠረት ይንቀሳቀሳሉ፥ አዋቂዎች ግን በፈቃዳቸው መሠረት ይንቀሳቀሳሉ። ምንም ዓይነት ስሜት ይሰማቸው አንድ ነገር የሚፈጽሙት ትክክል መሆኑን አረጋግጠው ነው። ያልበሰሉ ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ በኃጢአት የሚወድቁበት ምክንያት ውሳኔዎችን በስሜታቸው መሠረት በማድረጋቸው ነው። በፈተና «እምቢ» በማለት ወሳኝ እርምጃ በወሰድህ ቁጥር እግዚአብሔር የበለጠ ሕይወትህን ይቆጣጠራል። «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» (ፊል. 2፡13)። ሞት (1፡15)፡- ያለመታዘዝ ወይም ኃጢአት የሚወልደው ሞትን እንጂ ሕይወትን አይደለም። አንድ ኃጢአት ወደ መብሰል ደረጃ ለመድረስ ዓመታት ሊወስድ ይችላል። በሚበስልበት ጊዜ ግን ውጤቱ ሞት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ብናምንና ይህንን የመጨረሻ አሳዛኝ ነገር ብንመለከት ለፈተና እንዳንሸነፍ የሚያበረታታ ኃይል ይሆንልናል። እግዚአብሔር ስለሚወደን ይህንን መከላከያ ሰጥቶናል። «በውኑ ኃጢአተኛ ይሞት ዘንድ እፈቅዳለሁን?» (ሕዝቅኤል 18፡23)።

በፈተናና በኃጢአት ውስጥ ያሉት እነዚህ አራት ደረጃዎች በዘፍጥረት 3 በተመዘገበው የመጀመሪያው ኃጢአት ታሪክ በግልጽ ተመልክተዋል።

እባብ ሔዋንን ለመሳብ የተጠቀመበት ምኞትን ነበር። «ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ፥ እንደ እግዚአብሔር መልካምንና ክፉውን የምታውቁ እንደምትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ» (ዘፍ. 3፡5)። እውቀትን ማግኘት ክፉ የሚያደርገው አንዳች ነገር አለን? ምግብን መብላትስ ክፉ የሚያደርገው ነገር አለን? ሔዋንም «ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ አየች» (ዘፍ. 3፡6) ፍላጎቷም ተነሣሣ።

ጳውሎስ ስለ ሔዋን መታለል በ2ኛ ቆሮ. 11፡3 ላይ ገልጧል። «... ነገር ግን እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት አሳባችሁ ተበላሽቶ

ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ» ሰይጣን አታላይ ነውና አእምሮን ወይም አስተሳሰብን ለማታለል ይፈልጋል። ሔዋንን ለማጥመድ የተጠቀመበት ማባበያ እንዳይበላ የተከለከለው ዛፍ መልካምና የሚያስጎመጅ እንደሆነ፥ ከፍሬው መብላትም ጥበበኛ እንደሚያደርጋት አሳሰባት። ማባበያውን አየችና «... ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» የሚለውን የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ዘነጋች (ዘፍ. 2፡17)።

ሔዋን የዛፉን ፍሬ በመብላቷ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጣሰች። ፍሬውንም ለባሏ ሰጠችው። እርሱም በመብላቱ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጣሰ። አዳም ተታልሎ ሳይሆን ሆን ብሎ የሠራው ኃጢአት በመሆኑ ኃጢአቱ የሰውን ዘር አስጨናቂና አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ከተተው። (1ኛ ጢሞ. 2፡12-15 እና ሮሜ 5፡12-21 አንብብ።)

አዳምና ሔዋን ወዲያውኑ መንፈሳዊ ሞትን ሞቱ። (ከእግዚአብሔር ተለዩ።) በመጨረሻም ሥጋዊ ሞትን ሞቱ። በአዳም ምክንያት ሰዎች ሁሉ ሞቱ (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡21-22)። ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይቀበል የሚሞት ሰው ሁሉ የዘላለም ሞት ይጠብቀዋል ይህም የእሳት ባሕር ነው (ራእይ 20፡11-15)።

ከፈተና ጋር ፊት ለፊት በምትገናኝበት ጊዜ ዓይኖችህን ከሚያባብለው ማጥመጃ ላይ አንሳና አሻግረህ ኃጢአት የሚያስከትላቸውን ነገሮች አስብ። ይህም የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። «የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና» (ሮሜ 6፡23)።

የእግዚአብሔርን መልካምነት አስብ (1፡17)

ከጠላት የማታለያ ዘዴዎች አንዱ እግዚአብሔር አባታችን ለእኛ እንደማይጠነቀቅና እንደማይወደን እንከብካቤም እንደማያደርግልን እንድናስብ ማድረግ ነው። ሰይጣን ሔዋንን ያሳታት እግዚአብሔር በእርግጥ ቢወዳት ኖሮ ከተከለከለው ዛፍ እንድትበላ ይፈቅድ እንደነበር በመግለጽ ነበር። ኢየሱስንም በፈተናው ጊዜ ራብን ምክንያት በማድረግ «አባትህ የሚወድህ ከሆነ ለምን ተራብክ?» አለው። የእግዚአብሔር መልካምነት በፈተና ከመሸነፍ የሚጠብቀን ታላቅ መከላከያ ነው። እግዚአብሔር መልካም ስለሆነ ስለሚያስፈልጉን ነገሮች ከማንም ምንም (ሰይጣንንም ጨምሮ) መጠበቅ አያስፈልገንም። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ከምንመገብ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆነን ብንራብ ይሻለናል። የእግዚአብሔርንም መልካምነት መጠራጠር ከጀመርን

ሰይጣን በሚያቀርበው ነገር እንሳባለን። ደግሞም ተፈጥሮአዊ ፍላጎታችን በማጥመጃነት ለቀረበው መሳቢያ ይሸነፋል። ሙሴ እስራኤላውያንን በተስፋይቱ ምድር በረከት ሕሜት ሲያደርጉ (ዘዳ. 6፡10-15) የእግዚአብሔርን መልካምነት እንዳይዘነጉ አስጠንቅቆአቸው ነበር። እንዲህ ዓይነቱ ማስጠንቀቂያ ዛሬም ቢሆን ያስፈልገናል። ያዕቆብ ስለ እግዚአብሔር መልካምነት አራት ሐቆች አቅርቧል። - እግዚአብሔር የሚሰጠው መልካም ስጦታዎችን ብቻ ነው። - በዓለም ላይ የሚገኙ መልካም ነገሮች ሁሉ የተገኙት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። - ከእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር ግን መልካም አይደለም። - ከእግዚአብሔር የመጣ ነገር መልካምነቱን ወዲያውኑ ባናየውም እንኳ መልካም ነው። ጳውሎስ ለሥጋው መውጊያ እንዲሆን የሰጠው ነገር ከእግዚአብሔር የተቀበለው ስጦታ ነበር። ያልተለመደ ስጦታ ቢሆንም ለጳውሎስ እጅግ ከፍተኛ በረከት ሆኖለት ነበር (2ኛ ቆሮ. 12፡1-10)። - እግዚአብሔር ስጦታን የሚሰጥበት መንገድ መልካም ነው። - የዚህ ቁጥር ሁለተኛው ሐረግ «እግዚአብሔር ስጦታን የሚሰጥባቸው መንገዶች ሁሉ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አንድ ሰው ፍቅር የሌለው ስጦታ ሊሰጠን ይችላል። ስጦታው የተሰጠበት ሁኔታ የስጦታውን ዋጋ ሊያቀልለው ይችላል እግዚአብሔር ግን በረከትን የሚሰጠን በፍቅር፥ ጸጋና ቸርነት በሞላበት መንገድ ነው። የሚሰጠን ስጦታም ሆነ የአሰጣጡም ሁኔታ መልካም ናቸው።

- ያለ ማቋረጥ ይሰጠናል፡- «ከላይ ይመጣሉ» የሚለው ቃል የአሁን ጊዜ ሆኖ የማያቋርጥ ድርጊትን የሚያመለክት ነው። «ያለ ማቋረጥ ከላይ ይመጣል» የሚል ትርጉም ነው ያለው። እግዚአብሔር ስጦታውን የሚሰጠው አልፎ አልፎ ሳይሆን ሁልጊዜ ያለማቋረጥ ነው። ለጊዜው ባናያቸው እንኳ ስጦታዎቹን እየላከ ነው። ይህንን እንዴት እናውቃለን? እርሱ በቃሉ ስለነገረንና ቃሉንም ስለምናምን ነው።

- እግዚአብሔር አይለወጥም፡- በብርሃናት አባት ዘንድ የጨለማ ጥላዎች የሉም። እግዚአብሔር ይለወጥ ዘንድ አይቻለውም። እርሱ ቅዱስ ስለሆነ ወደ መጥፎነት ሊለወጥ አይችልም። እርሱ ከመጀመሪያው ጀምሮ ፍጹም ስለሆነ እየተሻሻለ ሊሄድ አይችልም። የፀሐይ ብርሃን የሚለዋወጠው ምድር በተዘዋወረች ቁጥር ነው። ፀሐይ ግን ማብራቷን አታቋርጥም። በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል ጥላ ቢያጠላ ምክንያቱ እግዚአብሔር አይደለም። እርሱ የማይለወጥ አምላክ ነው። ስለዚህ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ስንሆን ወይም ፈተና ሲገጥመን

የእግዚአብሔርን ፍቅር እውነተኛነት ልንጠይቅ ወይም መልካምነቱን ልንጠራጠር ጨርሶ አይገባንም።

ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሔርን መልካምነት ቢያስታውስ ኖሮ ከቤርሳቤህ ጋር ማመንዘርና አስከፊ ኃጢአቶችን መፈጸም ባልቻለ ነበር። ነቢዩ ናታን ለንጉሡ እንዲህ አለው፡- «የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በእስራኤል ላይ ንጉሥ ልትሆን ቀባሁህ። ከሳኦልም እጅ አዳንሁህ፥ የጌታህንም ቤት ሰጠሁህ፥ የጌታህንም ሚስቶች በብብትህ ጣልሁልህ። የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ፤ ይህም አንሶ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምርልህ ነበር» (2ኛ ሳሙኤል 12፡7-8)። በዚህ አጠር ያለ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሰጠሁህ የሚለው ቃል ምን ያህል እንደተደጋገመ ተመልከት። እግዚአብሔር ለዳዊት መልካም ነበር ዳዊት ግን የእግዚአብሔርን መልካምነት ዘነጋና በማባበያው ወጥመድ ውስጥ ገባ።

ፈተናን ለመቋቋም የሚረዳ የመጀመሪያ መከላከያ አሉታዊ የሆነው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። ሁለተኛው ደግሞ፥ አዎንታዊ ሲሆን ይህም የእግዚአብሔር መልካምነት ነው። እግዚአብሔርን መፍራት ጤናማ ዝንባሌ ቢሆንም የእግዚአብሔር ፍቅር ግን ከዚያ ልቆ መመዘን አለበት። እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የምንችለው ስለሚቀጣን ሊሆን ይችላል፤ ወይም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የምንችለው ለእኛ እጅግ ለጋሽ ስለሆነና በዚህም ምክንያት ስለምንወደው ሊሆን ይችላል።

ዮሴፍ በጌታው በጶጢፋር ሚስት በተፈተነ ጊዜ ኃጢአትን ከማድረግ የተቆጠበው በዚህ አዎንታዊ ዝንባሌ ምክንያት ነው (ዘፍ. 39፡7-23)። «... እነሆ ጌታዬ በቤቱ ያለውን ምንም የሚያውቀው የለም፥ ያለውንም ሁሉ ለእኔ አስረክቦኛል፥ ለዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰው የለም። ሚስቱ ስለሆንሽ ከአንቺም በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም፤ እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገርና ኃጢአት አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» (ዘፍ. 39፡8-9)። ዮሴፍ እነዚህ በረከቶች ሁሉ የመጡት ከእግዚአብሔር እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር። በፈተና ከመውደቅ የጠበቀው በአሠሪዎቹ በኩል የተቀበለው የእግዚአብሔር መልካምነት ነበር።

የእግዚአብሔር ስጦታ ሁልጊዜ ከሰይጣን የማታለያ ስጦታ የሚበልጥ ነው። ሰይጣን የሚሰጠው ምንም ዓይነት ስጦታ የለውም፤ ምክንያቱም በመጨረሻ እጅግ የናረ ከፍያን ይጠይቃል። «የእግዚአብሔር በረከት ባለጠጋ ታደርጋለች፥ ኃዘንም ከእርስዋ ጋር

አይጨመርም» (ምሳሌ 10:22)። አካን የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያና መልካምነቱን ረሳ፤ ስለዚህ የተከለከለውን ሀብት ተመለከተ፥ ተመኘና ወሰደው። በወሰደውም ነገር ሀብታም ሆነ፥ እርሱን ተከትሎ የመጣው ኃዘን ግን ሀብቱንና ብልጥግናውን ወደ ድኅነት ቀየረው (ኢያሱ 7)።

በሚቀጥለው ጊዜ ፈተና ሲገጥምህ እግዚአብሔር በሕይወትህ ያደረገውን መልካምነት አስላስል። አንድ ነገር እንደሚያስፈልግህ ካሰብክ እግዚአብሔር እንዲያሟላልህ በማመን ጠብቀው። በሰይጣን ማባበያ ወጥመድ ከቶ አትጫወት። «የፈተና አንዱ ዓላማ ትዕግሥትን እንድንማር ነው። ዳዊት ንጉሥ ሳኦልን በመግደል እርሱ የሚነግሥበትን ጊዜ እንዲያፋጥን ሁለት ጊዜ ተፈተነ። ፈተናውን በመቋቋም ግን የእግዚአብሔርን ጊዜ ጠበቀ።

የእግዚአብሔርን ውስጣዊ መለኮታዊ ተፈጥሮ አስብ (1:18)

በመጀመሪያ መከላከያ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ «ወደ ፊት አሻግረህ በመመልከት የፍርድን ነገር አስብ» የሁለተኛው መከላከያ ደግሞ «ዙሪያህን በመመልከት ለአንተ እንዴት መልካም እንደሆንኩ አስብ» ይላል። በሦስተኛው መከላከያ ላይ ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ «ወደ ራሳችሁ በመመልከት የተወለዳችሁት ከላይ እንደሆነና መለኮታዊ ተፈጥሮ እንዳላችሁ አስቡ» ይለናል።

ያዕቆብ መወለድን ወደ ኃጢአትና ሞት የሚመራ ምኞትን ለመግለጥ እንደ ምሳሌ ተጠቅሞበታል (1:15)። በተጨማሪ በኃጢአትና በፈተና ላይ ድልን በመለማመድ እንዴት ሐሤት እንደምናደርግ ለማስረዳትም ተጠቅሞበታል። ሐዋርያው ዮሐንስም በ1ኛ ዮሐ. 3:9 ላይ በተመሳሳይ አቀራረብ ተጠቅሞአል። በዚህ ስፍራ «ዘሩ» የሚለው ቃል በአማኝ ሕይወት ውስጥ ስላለው መለኮታዊ ሕይወትና ተፈጥሮ የሚናገር ነው። የዚህን ልደት ባሕርያት አስተውል።

መለኮታዊ ነው፡- ኒቆዲሞስ ዳግም ለመወለድ ወደ እናቱ ማኅፀን ተመልሶ መግባት እንዳለበት አሰበ፤ ይህ አስተሳሰብ ግን ስሕተት ነበር። ይህ ልደት በሥጋ የሚሆን ሳይሆን ከላይ የሚሆን ነበር (ዮሐንስ 3:1-7)። ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ሥጋዊ ልደታችንን ያመነጨን እራሳችን እንዳልሆንን ሁሉ መንፈሳዊ ልደታችንንም ልናመጣ አንችልም። እምነታችንን በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ

በምናደርግበት ጊዜ የዳግም ልደትን ተአምር የሚሠራ እግዚአብሔር ነው።

በጸጋ የተገኘ ነው፡- በጥረታችን ያገኘነው አይደለም፤ የሚገባን ስለሆነም አይደለም ያገኘነው። እግዚአብሔር መንፈሳዊ ልደትን የሰጠን በራሱ ጸጋና ፈቃድ ነው። «እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም (ከሰው ዘር)፥ ወይም ከሥጋ (በሰው ጥረት)፥ ወይም ከወንድ ፈቃድ (በሰው እርዳታ) አልተወለዱም (ዮሐ. 1፡13)። ማንም ሰው በዘመዶቹ፥ በአስተሳሰቡና በውሳኔው ወይም በሃይማኖቱ አማካይነት ዳግም ሊወለድ አይችልም። ዳግም (አዲስ) ልደት የእግዚአብሔር ሥራ ነው።

በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት የሚሆን ነው፡- ሰብአዊ ልደት በሁለት ወላጆች ምክንያት የሚፈጸም እንደሆነ ሁሉ መለኮታዊ ልደትም ሁለት ወላጆችን ይፈልጋል፤ እነዚህም የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ናቸው። «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው» (ዮሐ. 3፡6)። «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘለዓለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ» (1ኛ ጴጥ. 1፡23)። የእግዚአብሔር መንፈስ በእግዚአብሔር ቃል ተጠቅሞ የዳግም ልደትን ተአምር ይፈጽማል። የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና ኃይለኛ ስለሆነ (ዕብ. 4፡12) በክርስቶስ ባመነ ኃጢአተኛ ሰው ልብ ሕይወትን ያፈልቃል። ይህም ሕይወት የእግዚአብሔር ሕይወት ነው።

ጥራት ያለው ልደት ነው፡- «ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን» የተወለድን ነን። ያዕቆብ የሚጽፈው ለአይሁድ አማኞች ስለሆነ በኩራት የሚለው ቃል ጥልቅ ትርጉም አለው። በብሉይ ኪዳን ዘመን አይሁዶች ለእግዚአብሔር ራሳቸውን መስጠታቸውንና ታዛዥነታቸውን ለመግለጽ በኩራታቸውን ለእግዚአብሔር ያቀርቡ ነበር። «እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር፥ ከፍሬህም ሁሉ በኩራት» (ምሳሌ 3፡9)። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት በሙሉ ከፍተኛዎቹና ጥራት ያላቸው ፍጥረቶች ክርስቲያኖች ናቸው። የእግዚአብሔር ባሕርይ ተካፋይ ነን። በዚህም ምክንያት የሰይጣንን ማባበያና ማጥመጃ መቀበል ወይም ኃጢአተኛ የሆኑ ነገሮችን (ምኞቶችን) በማስተናገድ ክብራችንን ማቃለል የለብንም። ታላቅ ልደት፥ ታላቅ ሕይወትን ማስገኘት አለበት።

እግዚአብሔር አዲስ ልደትን ለእኛ በመስጠት አሮጌውን ልደት እንደማይቀበል አሳወቀ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር በኩሩን እየተወ ሁለተኛውን ልጅ ተቀብሎአል።ከቃየል ይልቅ አቤልን፥ ከእስማኤል ይልቅ ይስሐቅን፥ ከኤሳው ይልቅ ያዕቆብን ተቀበለ። በሰዎች ዓይን የቱንም ያህል የከበረ ቢሆንም እግዚአብሔር ዳግም መወለድ እንዳለብህ ይናገራል።

ፈተናን ድል እንድንነሣ የሚረዳን ይህ አዲስ ልደት ነው። አሮጌው ተፈጥሮአችን (ከመጀመሪያው ልደት የተገኘው) እንዲያሸንፍ ከፈቀድንለት እንወድቃለን። አሮጌው ተፈጥሮአችንን (ሥጋችንን) የተቀበልነው ከአዳም ነው። ዳሩ ግን አዳም በኃጢአት የወደቀ ሰው ነው። ለአዲሱ ተፈጥሮአችን ከተገዛን ግን የሚሳካልን እንሆናለን፤ ምክንያቱም ይህ አዲስ ተፈጥሮ የሚመጣው ድል ነሺ ከሆነው ከክርስቶስ ነው።

አንድ የእሑድ ትምህርት ቤት ተማሪ ነገሩን በቀላል ቋንቋ እንዲህ በማለት ገልጾታል፡- «ሁለት ሰዎች በልቤ ይኖራሉ፤ የቀድሞው አዳምና ኢየሱስ። ፈተና የልቤን በር ሲያንኳኳ ከሁለቱ አንዱ በሩን መክፈት አለበት። እንዲከፍት የምፈቅድለት አዳምን ከሆነ ኃጢአትን አደርጋለሁ። ስለዚህ እንዲከፍት የምፈቅድለት ኢየሱስን ነው፤ እርሱ ሁልጊዜ አሸናፊ ነውና!»

ይህ አዲስ ተፈጥሮ ጠንካራና በውጊያም ብርቱ እንዲሆን በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ አለበት። መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ልደት ለመስጠት በቃሉ እንደ ተጠቀመ ሁሉ መንፈሳዊ ጥንካሬንም ለመስጠት በቃሉ ይጠቀማል። «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፤ ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ» (ማቴ. 4፡4)።

ምንም ዓይነት ሰበብ ይኑረን ከራሳችን በስተቀር ስለ ኃጢአታችን ማንንም መውቀስ አንችልም። ወደ ፈተናና ኃጢአት የሚመራን የራሳችን ምኞት ነው። እግዚአብሔር በዚህ ሊወቀስ አይገባም። ይልቁኑ እግዚአብሔር ከኃጢአት ሊጠብቀን እነዚህን ሦስት መከላከያዎች ሰጥቶናል። መከላከያዎቹን በጥንቃቄ ካስተዋልንና ከጠበቅን አክሊልን እናገኛለን (1፡12)፤ መከላከያዎቹን ጥሰን ካለፍን ግን ሞት ይጠብቀናል፥ (1፡15)። የትኛውን እንመርጥ ይሆን?

(ያዕቆብ 1:19-27)

«ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ፥ ለቁጣም የዘገየ ይሁን፤ የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና። ስለዚህ ርኩሰትን ሁሉ የክፋትንም ትርፍ አስወግዳችሁ፥ ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁ የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ።

ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ። ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና። ወዲያውም እንደምን እንደሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነፃ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት ሥራውንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነ በሥራው የተባረከ ይሆናል።

አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢሆን የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው። ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች፥ ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፤ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነትን መጠበቅ ነው።»

እራስን ከማታለል እንቆጠብ

በዚህ ክፍል ትኩረት የተሰጠው ነገር እራስን የማታለል አደገኛነት ነው። «እራሳችሁን እያሳታችሁ» (ቁጥር 22) «ልቡን እያሳተ» (ቁጥር 26)። አንድ ክርስቲያን ሰይጣን ሲያታልለውና ኃጢአትን ቢሠራ አንድ ነገር ነው፤ ነገር ግን እራሱን እያታለለ ኃጢአትን የሚያደርግ ከሆነ ከመጀመሪያው የበለጠ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ገብቷል ማለት ነው።

ብዙ ሰዎች ደኅንነትን ሳያገኙ ደኅንነት እንዳገኙ አድርገው በማሰብ እራሳቸውን ያታልላሉ። «በዚያ ቀን ብዙዎች፦ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንም? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል፥ የዚያን ጊዜ፦ ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ» (ማቴዎስ 7፡22-23)።

ስለ ክርስትና ኑሮአቸው እራሳቸውን የሚያታልሉ እውነተኛ ክርስቲያኖችም አሉ። መንፈሳዊ ሳይሆኑ መንፈስዊ የሆኑ ይመስላቸዋል። አንድ ሰው በግልጽነትና በታማኝነት ራሱን ማወቅና ችግሩንም መገንዘቡ የመብሰሉ አንዱ ምልክት ነው። «ሀብታም ነኝና ባለጠጋም ሆኜአለሁ አንድ ስንኳ አያስፈልገኝም» (ራእይ 3፡17) የሚል ግን ብስለት የሌለው ሰው ነው።

መንፈሳዊ እውነታ ከእግዚአብሔር ጋር በቃሉ አማካይነት የሚደረግ የትክክለኛ ግንኙነት ውጤት ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው (ዮሐንስ 17፡17)። ከእግዚአብሔር እውነት ጋር በትክክለኛ መንገድ ግንኙነት ካደረግን ታማኝነት የጎደለን ወይም ግብዞች አንሆንም።

በእነዚህ ቁጥሮች ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ቃል ያለብንን ሦስት ኃላፊነቶች ይናገራል። እነዚህን ኃላፊነቶች በሚገባ ብንወጣ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር በታማኝነት መኖር እንችላለን።

ቃሉን መቀበል (1፡19-21)

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔርን ቃል «በውስጣችሁ የተተከለውን ቃል» (ቁጥር 21) ብሎ ይጠራዋል። ይህም ማለት

«የተዘራ ቃል» እንደማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ ስለ ዘሪው የተናገረውን ምሳሌ በመጠቀም (ማቴዎስ 13፡1-9 ና 18-23) የእግዚአብሔርን ቃል ከዘር፥ የሰውን ልብ ደግሞ ዘሩ ከሚዘራበት መሬት ጋር ያወዳድረዋል። ጌታ ኢየሱስ ስለ ዘሪው በተናገረው ምሳሌ አራት ዓይነት ልቦች እንዳሉ ይናገራል። እነዚህም ቃሉን የማያስተውል ወይም የማይቀበል በዚህም ምክንያት ፍሬ የማያፈራ ጠንካራ ልብ፥ በጣም ስሜታዊ የሆነ ነገር ግን ጥልቀት ስለሌለው ፍሬ የማያፈራ ልብ፥ በብዙ ነገሮች የተያዘና ንስሐ ባለማድረግ ቃሉ እንዳያፈራ ማነቆ የሚሆንበት ልብ እና ቃሉን ተቀብሎ ሥር እንዲሰድድ ብዙ ፍሬም እንዲያፈራ ምቹ የሆነ ልብ ናቸው።

የደኅንነት የመጨረሻ መመዘኛ ፍሬ ማፍራት ነው። ይህ ማለት የተለወጠ ሕይወት፥ ክርስቲያናዊ ባሕርይና አካሄድ ለእግዚአብሔር ክብር ለሌሎች የሚደረግ አገልግሎት ነው። ይህ ፍሬ ነፍሳትን ለክርስቶስ መማረክ (ሮሜ 1፡16)፤ በተቀደሰ ሕይወት ማደግ (ሮሜ 6፡22)፤ ቁሳዊ ንብረትን ማካፈል (ሮሜ 15፡28)፤ መንፈሳዊ ባሕርይ (ገላ. 5፡22-23)፤ መልካም ሥራዎች (ቆላ. 1፡10) እና እግዚአብሔርንም ማመስገን እንኳ (ዕብ. 13፡15) ሊሆን ይችላል። ሃይማኖታዊ ተግባራት ሊያሳዩ ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ሕይወት የሌላቸውና ለእግዚአብሔር ክብር የማይሆኑ ናቸው። እውነተኛ ፍሬ ሌላ ፍሬን ለማፍራት የሚችል ዘርን በውስጡ ይይዛል። ስለሆነም እርሻው ፍሬ ማፍራቱን፥ ደጋግሞ ማፍራቱን፥ የበለጠ ማፍራቱን ይቀጥላል (ዮሐ. 15፡1-5)

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል በትክክለኛ መንገድ ካልተቀበልነው በስተቀር በሕይወታችን ሊሠራ አይችልም። ኢየሱስ «ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ» (ማርቆስ 4፡24) አለ። ደግሞም በተጨማሪ «እንዴት እንድትሰሙ ተጠበቁ» (ሉቃ. 8፡18) አለ። ብዙ ሰዎች ኢየሱስ «... እያዩ ስለማያዩ፥ እየሰሙም ስለማይሰሙ፥ ስለማያስተውሉም ...» በማለት በተናገረለት አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ነው ያሉት (ማቴ. 13፡13)። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሚሰጥባቸውን ክፍሎችም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችን ይካፈላሉ። ነገር ግን ዕድገት ጨርሶ አይታይባቸውም። የአስተማሪው ወይም የሰባኪው ስሕተት ነውን? ምናልባት ሊሆን ይችላል፤ ደግሞም የአዳማጮቹም ስሕተት ሊሆን ይችላል። በዕብራውያን 5፡11 እንደተጻፈው በመንፈሳዊ ሕይወት መድከም ምክንያት የሰዎች ጆሮ ሊፈዝ ይችላል።

የቃሉ ዘር በልባችን ውስጥ እንዲዘራ ከፈለግን ያዕቆብ የሚሰጠንን መመሪያዎች መከተል አለብን።

ለመስማት የፈጠነ (1፡19)፡- «የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ» (ማቴ. 13፡9)። «እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው፥ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10፡17)። አንድ አገልጋይ የአሠሪውን ድምፅ፥ አንዲት እናት የሕፃን ልጇን አነስተኛ የልቅሶ ድምፅ ለመስማት ፈጣን እንደሆኑ ኣማኝም እግዚአብሔር የሚለውን ነገር ለመስማት ፈጣን መሆን አለበት።

ይህንን እውነት ግሩም በሆነ መንገድ የሚያስረዳ ምሳሌ ከንጉሥ ዳዊት ሕይወት እንመለከታለን (2ኛ ሳሙኤል 23፡14-17)። ዳዊት የፍልስጥኤማውያን ጭፍራ በቤተልሔም ሰፍረው በነበረበት ጊዜ በምሽግ ውስጥ ተደብቆ ነበር። በዚያም እያለ በልጅነቱና በወጣትነቱ ብዙ ጊዜ ተመላልሶበት ከነበረው ከቤተልሔም ምንጭ ቀዝቃዛ ውኃ የሚያጠጣው ሰው ለማግኘት ተመኘ። ይህንንም ምኞቱን በውስጡ ለራሱ ተናገረ እንጂ ለማንም ትእዛዝ አልሰጠም ነበር። «... በበሩም አጠገብ ካለችው ከቤተልሔም ምንጭ ውኃ ማን ባጠጣኝ? ብሎ ተመኘ» (2ኛ ሳሙኤል 23፡15)። ሦስቱም ኃያላን የንጉሡን ምኞት ሰሙና ሕይወታቸውን አደጋ ላይ በመጣል በፍልስጥኤማውያን ሠራዊት መካከል አልፈው ውኃውን አመጡለት። እነዚህ ሦስት የዳዊት ኃያላን «ለመስማት ፈጣን» ነበሩ።

ለመናገርም የዘገዩ (1፡19)፡- አንድ አፍና ሁለት ጆሮዎች አሉን። ይህም ከመናገር ይልቅ ለመስማት የፈጠንን መሆን እንዳለብን ያሳያል። ብዙ ጊዜ አፍ አውጥተን በንግግር ባንገልጸውም በልባችንና በአእምሮአችን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እንከራከራለን። «ከንፈሩን የሚገታ ግን አስተዋይ ነው» (ምሳሌ 10፡19)። «ጥቂት ቃልን የሚናገር አዋቂ ነው» (ምሳሌ 17፡27)። በሉቃስ 10፡29 ላይ የምንመለከተው ሕግ አዋቂ ከመናገር መቆጠብ ሲገባው «ባልንጀራዬ ማነው?» በማለት ከኢየሱስ ጋር ሲከራከር እንመለከተዋለን። በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ይካሄዱ የነበሩ የወንጌል ስብሰባዎች ሥርዓት አልነበራቸውም። ብዙ ጊዜ አዳማጮቹ ከተናጋሪዎቹ ጋር ይከራከሩ ነበር። ያዕቆብ በሚጽፍላቸው ወንድሞች መካከል እንኳ ጦርነትና ጠብ ነበር (ያዕቆብ 4፡1)።

ለቁጣ የዘገየ (1፡19)፡- በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ ልንቆጣ አይገባም። «ለትዕግሥተኛ ሰው ብዙ ማስተዋል አለው። ቁጡ ግን ስንፍናውን ከፍ ከፍ ያደርጋል» (ምሳሌ 14፡29)። ነቢዩ ናታን ለዳዊት ሀብታሙ ሰው ከድሀው ስለቀማው አንዲት ትንሽ በግ ታሪክ በነገረው

ጊዜ ንጉሡ እጅግ ተቆጣ፤ የተቆጣው ግን ይህን በደል የፈጸመው ሌላ ሰው እንደሆነ በማሰብ ነበር። ነቢዩ ናታንም ዳዊትን «ያ ሰው አንተ ነህ» አለው። ዳዊትም «እግዚአብሔርን በድያለሁ» በማለት ኃጢአቱን ተናዘዘ (2ኛ ሳሙ.12)። ጴጥሮስ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ለመስማት የዘገየ፤ ለመናገር የፈጠነና ለመቆጣት ችኩል በመሆኑ የሰው ነፍስ በሰይፍ ከማጥፋት የዳነው እጅግ ለጥቂት ነው። ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነሡ ግጭቶች የትዕግሥት ማጣትና ፈጥኖ የመናገር ውጤቶች ናቸው። በእርግጥ እግዚአብሔርን ከመፍራት የመነጨ በኃጢአት ላይ የሚደረግ ቁጣ አለ (ኤፌ. 4:26)። ጌታን የምንወደው ከሆነ ኃጢአትን መጥላት አለብን (መዝ. 97:10)። የሰው ቁጣ ግን የእግዚአብሔርን ጽድቅ አያመጣም (ያዕ. 1:20)። እንዲያውም ቁጣ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሕይወታችን እየበሰልን ስንሄድ እንድናፈራው የሚፈልገው የትዕግሥት ተቃራኒ ነው (ያዕ. 1:3-4)።

በአንድ ወቅት እንዲህ የሚል በግድግዳ ላይ የሚለጠፍ ጽሑፍ አየሁ። «ቁጣ እጅግ ዋጋ ያለው ነገር ነው። ነገር ግን ራስን ባለመግዛት የሚደረግ ቁጣ አሳፋሪ ነው» ለብረት ጥንካሬን የሚሰጠው እሳት ነው። በኃጢአት ላይ የማይቆጣ ሰው ከኃጢአት ጋር መታገል አይችልም። ኃጢአታችንን በግልጽ የሚያሳየን የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስለዚህም በእግዚአብሔር ቃል እንዳንቆጣ ያዕቆብ ያስጠነቅቀናል። በመስተዋት ውስጥ ያየውን የራሱን ምስል በመጥላት መስተዋቱን እንደሰበረው ሰው ሁሉ አንዳንዶች ስለ እነርሱና ስለ ኃጢአቶቻቸው እውነት በሚናገረው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ይቆጣሉ።

የተዘጋጀ ልብ (1:21)፡- ያዕቆብ የሰውን ልብ እንደ አንድ የእርሻ ቦታ ይመለከተዋል። አንድ የእርሻ ቦታ በቂ እንክብካቤ ካልተደረገለት የሚያበቅለው ዐረም ብቻ ነው። ዐረሙን እንድንነቅልና እንደ መሬት የሆነው ልባችንን ለእግዚአብሔር ቃል ዘር እንድናዘጋጅ አጥብቆ ይጠይቀናል። «የክፋትንም ትርፍ» የሚለው ሐረግ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ የሆነ ዐረም የበቀለበትን መሬት የሚያሳይ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ባልተዘጋጀ ልብ ለመቀበል መሞከር ሞኝነት ነው።

እንደ መሬት የሆነ ልባችንን ለእግዚአብሔር ቃል የምናዘጋጀው እንዴት ነው? በመጀመሪያ ኃጢአታችንን በመናዘዝ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ይቅርታን በመጠየቅ (1ኛ ዮሐንስ 1:9) ቀጥሎም የእግዚአብሔርን ፍቅርና ጸጋ በማሰላሰል በልባችን ያለውን ማንኛውንም

ደንዳናነት እንዲነቅልና ለእርሻ እንደሚዘጋጅ መሬት አድርጎ እንዲያስተካክልልን በመጠየቅ ነው። «ጥጋቱን እርሻ እረሱ፥ በእሾህም ላይ አትዝሩ» (ኤር. 4፡3) በመጨረሻም የየዋህነት ዝንባሌ ማሳየት አለብን (ያዕቆብ 1፡21)። የዋህነት በቁጥር 19 ና 20 የተገለጠው የቁጣ ተቃራኒ ነው። ቃሉን በየዋህነት በምትቀበልበት ጊዜ ያለምንም ክርክር ከቃሉ ጋር ትስማማለህ። እንደ እግዚአብሔር ቃልነቱም ታከብረዋለህ ከራስህ አስተሳሰብ ጋር እንዲስማማ ብለህ አታጣምመውም።

በውስጣችን የተተከለውን ቃል የማንቀበል ከሆነ እራሳችንን እናታልላለን። የተለያዩ አመለካከቶች ላይ የሚከራከሩ ክርስቲያኖች እራሳቸውን ያሞኛሉ። ውይይታቸው ለመንፈሳዊ ዕድገት የሚጠቅም እንደሆነ ሊያስቡ ይችላሉ። እውነታው ሲታይ ግን ዐረምን ብቻ ነው እያበቀሉ ያሉት።

ቃሉን ማድረግ (1፡22-25)

ቃሉን መስማት ብቻ በቂ አይደለም፤ ልናደርገውም ይገባል። ብዙ ሰዎች ጥሩ መልእክት መስማት ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት ለዕድገት እንደሚረዳቸውና የእግዚአብሔርን በረከት እንደሚያስገኝላቸው በማሰብ ይሳሳታሉ። በረከትን የሚያመጣው መስማት ሳይሆን ማድረግ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ላይ የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀምና በማሳመር ምልክቶች ያደርጋሉ፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳቸው በእነርሱ ላይ ምንም ምልክት አያደርግም። የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ብቻ መንፈሳዊ እንደሆንክ የምታስብ ከሆነ እራስህን እያታለልክ ነው።

ያዕቆብ ከዚህ ቀደም ብሎ በነበረው አንቀጽ የእግዚአብሔርን ቃል ከዘር ጋር አወዳድሮ ነበር። በዚህ አንቀጽ ደግሞ ከመስተዋት ጋር ያወዳድራል። ከዚህ ሌላ የእግዚአብሔርን ቃል እንደመስተዋት አድርገው የሚያቀርቡ ሌሎች ሁለት ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህ ሦስት ጥቅሶች በአንድነት አያይዘን ስናያቸው የእግዚአብሔር ቃል እንደ መስተዋት ሆኖ የሚሰጠውን ሦስት የተለያዩ አገልግሎቶቹን እንገነዘባለን።

መመርመር (1፡23-25)፡- አንድ ሰው መስተዋት እንዲኖረው የሚያደርግበት አንዱ ዋና ዓላማ እራሱን ለማየትና በተቻለ መጠን አንዳችም ጉድፍ የሌለበት ንጹሕ ሰው ሆኖ ለመገኘት ነው። በእግዚአብሔር ቃል መስተዋትነት እራሳችንን በምንመለከትበት ጊዜ

በትክክል ምን እንደምንመስል እናውቃለን። ያዕቆብ፥ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መስተዋት በሚመለከቱበት ጊዜ የሚሠሩትን ጥቂት ስሕተቶች ይጠቅሳል።

በመጀመሪያ፥ እራስን በመስተዋት እንደ ቀልድ አይቶ ማለፍ ነው። ቃሉን በሚያነቡበት ጊዜ በጥንቃቄ አያጤኑትም። ብዙ እውነተኛ አማኞች በየቀኑ ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው አንዳንድ ምዕራፍ ያነብባሉ። ይህንን የሚያደርጉት ሃይማኖታዊ ሥርዓት ሆኖባቸው ብቻ ስለሆነ አንዳችም ጥቅም አያገኙም። የየዕለት ምንባባቸውን ካላነበቡ ጎሊናቸው ያስጨንቃቸዋል። ጎሊናቸውን ሊያስጨንቅ የሚገባው ቃሉን በንዝህላልነት ማንበባቸው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስን ላይ ላዩን እንደ ቀልድ ማንበብ ውስጣዊ ችግራችንን ጨርሶ አይገልጥም። ይህ በፎቶግራፍና በራጅ መካከል ያለውን ልዩነት ይመስላል።

ሁለተኛው ስሕተት ደግሞ፥ በመስተዋት ያዩትን መርሳት ነው፡- ወደ ልባቸው ውስጠኛ ክፍል በሚገባ ተመልክተው ቢሆን ኖሮ የተመለከቱት ነገር አይረሱትም ነበር። ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በነበረበት ጊዜ በነበሩ፥ «አክራሪዎች» ለመሳቅ ብዙ ጊዜ ይቃጣናል። ነገር ግን ከእነዚህ ሰዎች አንዳንድ ነገር ለመማር በቻልን ነበር። ጆን ዌስሊ ስለ ስብከት አገልግሎት እንደዚህ በማለት ጽፎአል፡- «አንዱ ከእኔ በፊት እንደሞተ ሰው ሆኖ ወደቀ፤ ሁለተኛውና ሦስተኛውም እንደዚሁ ወደቁ። ግማሽ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሌሎች አምስት ወደቁ። ከእነዚህ አብዛኛዎቹ በጥልቅ ስቃይ ውስጥ ነበሩ። (በሰኔ 22/1739 ዓ.ም. የወጣ የዌስሊ ማስታወሻ)። እነዚህ ሰዎች የሥነ ልቡና ችግር ነበረባቸው ከማለት ይልቅ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በልባቸው ለተረዱት እውነተኛ እውቀት የሰጡትን ምላሽ እንመልከት። ኢሳይያስ፡- «ጠፍቻለሁና ወዮልኝ» (ኢሳይያስ 6፡5) በማለት ጮኸ። ጴጥሮስ ደግሞ፡- «እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ራቅ አለ (ሉቃ. 5፡8)። ኢዮብ በዘመኑ ከነበሩ ሰዎች ሁሉ የተሻለ ጻድቅ ሰው ነበር። ነገር ግን እንዲህ በማለት ኃጢአቱን ተናዘዘ፡- «ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ» (ኢዮብ 42፡6)።

ሦስተኛው ስሕተት ደግሞ፥ ቃሉ እንዲያደርጉት የጠየቃቸውን ነገር ያለማድረጋቸው ነው። «መስማት ከማድረግ ጋር አንድ ዓይነት እንደሆነ ይገምታሉ» ነገር ግን አንድ አይደሉም። እኛ ክርስቲያኖች ማንበብን «የማድረግ» ወይም መናገርን «የማድረግ» ምትክ አድርገን እናቀርባለን። ማለቂያ የሌላቸው በወንጌል ስርጭት ስለ ቤተ ክርስቲያን

ዕድገት በተዘጋጀ አጠቃላይ ስብሰባዎችና የኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ እንገኛለን፤ በዚህ ዕድገት ያገኘን ይመስለናል። በመሠረቱ ስብሰባዎችንና የኮሚቴ ስብሰባዎችን ማካሄድና ማካፈል ስሕተት አይደለም፤ ከዚያ በኋላ አለማገልገል ግን ኃጢአት ነው።

የእግዚአብሔርን መስተዋት ለእኛ በሚጠቅም መንገድ እንድንገለገልበት ከፈለግን በጽኑ ዓላማና በጥንቃቄ ልናተኩርበት ያስፈልጋል (ያዕቆብ 1:25)። በፍጥነት ላይ ላዩን ማየት ሳይሆን ልባችንና ሕይወታችንን በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን መመርመር አለብን። ይህም ጊዜን፥ በቂ ትኩረትንና እውነተኛ መሰጠትን የሚጠይቅ ነው። በየዕለቱ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው አምስት ደቂቃ ለጠለቀ መንፈሳዊ ሕይወት እራስን ለመመርመሪያ በቂ ሊሆን አይችልም።

በዓመታት ሁሉ ውስጥ ለጤንነቴ እንክብካቤ ስላደረጉልኝ ሐኪሞች ዕድለኛ ነኝ፤ ለእነርሱም ባለ ዕዳ ነኝ። ከእያንዳንዳቸው የማደንቀው ሁለት ቁም ነገር ነበራቸው። እያንዳንዳቸው ሳይጣደፉ ከእኔ ጋር ጊዜ ያጠፉ ነበር። ሁልጊዜም እውነቱን ይነግሩኝ ነበር። ታላቁ ሐኪም ኢየሱስ (ማቴ. 9:12) የሚመረምረን በቃሉ አማካይነት ነው። ሥራውን በሚገባ እንዲሠራም በቂ ጊዜ እንድንሰጠው ይፈልጋል፤ ቃሉን በጥልቀትና በጥንቃቄ መመልከት ሲገባን በፍጥነትና ላይ ላዩን ብለን የምናልፈው እንዳናየው የምንፈልገው ነገር ስላለ ይሆናል።

እራሳችንን ከተመለከትን በኋላ ምን እንደሆንንና እግዚአብሔር ምን እንዳለ በማስታወስ ቃሉ እንዳለን ማድረግ አለብን። በረከት የሚመጣው ቃሉን በማድረግ እንጂ በማንበብ አይደለም። የምዕራፍ 1 ቁጥር 25 ቀጥተኛ ትርጉም «ይህ ሰው በሥራው ይባረካል» የሚል ነው። የያዕቆብ መጽሐፍ ትኩረት የእግዚአብሔርን ቃል በማድረግ ላይ ነው። ቃሉን ካነበብን በኋላ በሥራ መተርጎማችንን መቀጠል አለብን። (ያዕቆብ 1:25ና ይህ ጉዳይ በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይከናወን እንደ ነበር ለማየት የሚጠቅሙ ምሳሌዎችን ከሚቀጥሉት ጥቅሶች ተመልከት የሐዋ. 1:14፤ 2:42 ና 46፤ 13:43፤ 14:22 ና 26:22)።

ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ቃል «ነፃ የሚያወጣ ፍጹም ሕግ» (ቁጥር 25) ብሎ የጠራው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ለቃሉ በምንታዘዝበት ጊዜ እግዚአብሔር ነፃ ስለሚያወጣን ነው። «ትእዛዛትህንም ፈልጌአለሁና፤ አስፍቼ እሄዳለሁ» (መዝሙር 118:45)። «ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው»

(ዮሐንስ 8፡34)። «... እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፥ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው» (ዮሐንስ 8፡31-32)።

መመርመር፡- እንደ መስተዋት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል የመጀመሪያው አገልግሎት ግን መመርመር ነው። ሁለተኛ አገልግሎትም ደግሞ አለ።

ንጽሕና (ዘጸአት 38፡8)፡- የመገናኛውን ድንኳን ከሠራ በኋላ ሙሴ ናስ የሚመስሉ የሴቶች መስተዋቶችን ወሰደና የመታጠቢያውን ሰሐንና መቀመጫውን ሠራበት። ይህ የነሐስ መታጠቢያ መሥዋዕት በሚሠዋበት በነሐስ መሠዊያውና ቅድስት በተባለው ስፍራ መካከል የሚቀመጥ ነበር። (ለዝርዝር ጉዳዩ ዘጸአት 30፡17-21 አንብብ።) ይህ የነሐስ መታጠቢያ በውኃ የተሞላ ሲሆን ካህናት ወደ ቅድስት ከመግባታቸውና አገልግሎትን ከመስጠታቸው በፊት እጃቸውንና እግራቸውን በዚህ ይታጠቡ ነበር።

ለመታጠብ የሚያገለግል ውኃ የማንጻት ኃይል ያለው የእግዚአብሔር ቃል ምልክት ነው። «እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ» (ዮሐንስ 15፡3)። ቤተ ክርስቲያን የተቀደሰችውና የነጻችው «በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር» ነው (ኤፌ. 5፡26)። አንድ አማኝ ለአንዴና ለመጨረሻ ታጥቦ የነጻው በክርስቶስ ባመነበት ጊዜ ነው (1ኛ ቆሮ. 6፡9-11፤ ቲቶ 3፡4-6)። ነገር ግን በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ እጆቹና እግሮቹ ስለሚቆሽሹ መንጻት ያስፈልገዋል (ዮሐንስ 13፡1-11)።

እንደ መስተዋት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል እኛን በመመርመር ኃጢአታችንን ለመግለጥ ብቻ ሳይሆን ለማንጻትም ያገለግለናል። የመንጻትም ተስፋ ይሰጠናል፤ (1ኛ ዮሐንስ 1፡9) ቃሉን ባሰላሰልን ቁጥር ከመንፈሳዊ እድፈት ልባችንንና አእምሮአችንን ያነጻል። ጥልቅ በደላችንን የሚያስወግድልን የክርስቶስ ደም ነው። የቃሉ ውኃ ግን እድፈታችንን ለማጥራት ይጠቅመናል።

በ2ኛ ሳሙኤል 12 ነቢዩ ናታን ከዳዊት ጋር ያሳለፈው ኑሮ ይህንን እውነት ለማስረዳት የሚጠቅም ነው። ናታን ለዳዊት ስለተሰረቀችው ትንሽ ጠቦት ታሪክ ነገረው። ዳዊትም በዚህ ኃጢአት እጅግ ተቆጣ። ነቢዩ ናታን «ያ ሰው አንተ ነህ» ብሎ ለዳዊት በመናገር እንደመስተዋት በሆነው የእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ዳዊት እራሱን እንዲያይ አደረገ። ውጤቱም ኑዛዜና ንስሐ ሆነ፡- «እግዚአብሔርንም በድያለሁ»

አለ። እንደ መስተዋት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል የመመርመር ሥራውን ሠራ።

ነቢዩ ናታን ተግባሩን እዚህ ላይ አላቆመም። የእግዚአብሔርን ቃል ዳዊትን ለማንጻትም ተጠቅሞበታል። «እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፤ አትሞትም» አለው (2ኛ ሳሙኤል 12፡13)። ይህ ይቅርታን የማግኘትና የመንጻት ዋስትና ሲሆን የመጣውም ከቃሉ ነው። ዳዊት የነሐስ መታጠቢያውን ወዳለበት በመሄድ እጆቹንና እግሮቹን ታጠበ ማለት ነው።

እንደ መስተዋት የሆነው የቃሉ የመጀመሪያ ሁለት አገልግሎቶች የሆኑትን በመመርመርና እንደገና በመጠገን ላይ ብቻ ከቆምን ቃሉ የሚሰጠውን ሙሉ ጥቅም ሳናገኝ እንቀራለን። ስለዚህ ወደ ሦስተኛው የቃሉ አገልግሎት እንገባለን።

ከክብር ወደ ክብር መለወጥ (2ኛ ቆሮ. 3፡18)፡- ጌታ ካደሰን በኋላ በጸጋው በማደግ ተመልሰን ያንን ኃጢአት አንዳንሠራ ሊለውጠን ይፈልጋል። ብዙ ክርስቲያኖች ኃጢአታቸውን በመናዘዝ የእግዚአብሔርን ምሕረት እንደተቀበሉ ያስባሉ። ነገር ግን እኔነትንና ኃጢአትን በማሸነፍ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሲያድጉ አይታዩም።

በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 የቀደመው ኪዳን አገልግሎት በነበረው በሕግና የአዲሱ ኪዳን አገልግሎት በነበረው በጸጋ መካከል ያለውን ግንኙነት በማነጻጸር አቅርቦአቸዋል። ሕግ በጽላት ላይ የተጻፈ ሲሆን፥ ደኅንነት ማለት ግን የእግዚአብሔር ቃል በልባችን ሲጻፍ ማለት ነው። የቀድሞው ኪዳን አገልግሎት የሚኮንንና የሚገድል ሲሆን፥ የአዲስ ኪዳን አገልግሎት ግን ይቅርታንና ሕይወትን የሚያመጣ ነው። የሕግ ክብር ቀስ በቀስ እየከሰመ ሲሄድ የእግዚአብሔር ክብር ጸጋ ግን እየደመቀና እየፈካ የሚሄድ ነው። ሕግ ጊዜያዊ ሲሆን አዲሱ የጸጋ ኪዳን ግን ዘላለማዊ ነው።

ጳውሎስ ይህንን እውነት ለመግለጥ የተጠቀመው ሙሴንና ፊቱን የሸፈነበትን መጋረጃ ነው። ሙሴ እግዚአብሔርን ከተገናኘበት ተራራ በሚወርድበት ጊዜ ፊቱ ያንጸባርቅ ነበር (ዘጸአት 34፡29-35)። ሙሴ አይሁዶች ይህ ክብር እየደበዘዘ ሲሄድ እንዲያዩ አልፈለገም። ስለዚህም ከሕዝቡ ለመደበቅ በፊቱ ላይ መሸፈኛ አደረገ። ወደ ተራራው በሚመለስበት ጊዜ ግን መሸፈኛውን ይገልጥ ነበር። ኢየሱስ በሚሞትበት ጊዜ በቤተ መቅደስ የነበረው መጋረጃ ለሁለት በመቅደድ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን ግድግዳ

አስወገደ። የብሉይ ኪዳን ነቢይ እየደበዘዘ የሚሄደው ክብሩን ለመደበቅ መሸፈኛ ያደርግ ነበር። የአዲስ ኪዳን አማኝ ግን ያልተሸፈነ ፊት አለው፤ ክብሩም ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ይሄዳል።

2ኛ ቆሮ. 3፡18ን በዚህ መልክ መግለጥ ይቻል ይሆናል። «የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መስተዋት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ሲመለከት የእግዚአብሔርን አንድያ ልጅ (ኢየሱስ ክርስቶስን) ያያል፤ የእግዚአብሔርን ክብር ለመካፈልም በእግዚአብሔር መንፈስ ይለወጣል።» መለወጥ ብለን በአማርኛችን የተረጎምነው ቃል የግሪኩ አሳብ በውስጣዊ ለውጥ ምክንያት በውጭ የሚገለጥ ለውጥ ማለት ነው። አንዲት አስቀያሚ የሆነች ትል(አባጨጓሬ) እጅግ ወደምታምር ቢራቢሮ ትለወጣለች። ይህ ለውጥ ከላይ የገለጥነውን ለውጥ የሚያስረዳ ነው። አንድ አማኝ የእግዚአብሔርን ቃል ለመመልከት በቂ ጊዜ ሲወስድና በቃሉ ውስጥ ክርስቶስን ሲያይ ከክብር ወደ ክብር ይለወጣል። በውስጡ ያለው ክብር በውጭም ይገለጣል።

በማቴዎስ 17፡2፥ «በፊታቸውም ተለወጠ» ተብሎ የተተረጎመው ይህ ቃል ነው። በዚህ ተራራ ላይ የክርስቶስ ክብር ከውስጥ ወደ ውጭ አበራ። ይህንኑ ቃል በሮሜ 12፡2 ላይ እናገኘዋለን፥ «በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ» ይላል። የእግዚአብሔርን ቃል በምናሰላስልበት ጊዜ መንፈሱ አእምሮአችንን በማደስ የእግዚአብሔርን ክብር ይገልጥልናል። በአንድ ቀን መንፈሳዊ ክርስቲያኖች ለመሆን አንችልም። ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ መስተዋት በሆነው ቃሉ አማካኝነት የሚሠራው የሂደት ሥራ ነው።

በጣም አስፈላጊው ነገር ምንም ሳንደብቅ ሁሉን ግልጽ ማድረግ አለብን። መሸፈኛውን አንሡ። «አቤቱ፥ መርምረኝ ልቤንም እወቅ፤ ፍተነኝ መንገዴንም እወቅ፤ በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ፤ የዘላለምንም መንገድ ምራኝ» (መዝሙር (139)፡23-24)። «ኃጢአት የለብንም ብንል እራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐንስ 1፡8)።

የመጀመሪያው ኃላፊነታችን ቃሉን መቀበል ነው። ቀጥሎ ቃሉን ልናደርግ ይገባል፤ አለበለዚያ እራሳችንን እናስታለን። ይህም ወደ ሦስተኛው ኃላፊነት ይመራናል።

ቃሉን ማካፈል (1፡26-27)

በዚህ ስፍራ ሃይማኖት ተብሎ የተተረጎመው ቃል «በውጫዊ ተግባር የሚገለጥ ለአግልክት የሚሰጥ አገልግሎት» ማለት ነው። በአጠቃላይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው አምስት ጊዜ ብቻ ነው። (በያዕቆብ 1፡26-27፤ የሐዋ. 26፡5 ና ቆላስይስ 2፡18 ውስጥ ቃሉ «ግምለክ» ተብሎ ተተርጉሞአል።) ንጹሕ ሃይማኖት ከሃይማኖታዊ ሥርዓቶች፥ ከቤተ መቅደሶች ወይም ከልዩ ቀኖች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ንጹሕ ሃይማኖት ማለት የእግዚአብሔርን ቃል በተግባር ላይ ግዋል፥ በንግግርና በአገልግሎት ቃሉን ለሌሎች ማካፈልና ከዓለም መለየት ነው።

ንግግር (1፡26)፡- ያልተገታ ንግግር በዚህ ጉባኤ መካከል ከፍተኛ ችግር እንደ ነበረ የሚያሳዩ ብዙ ገለጻዎች በዚህ መልእክት ተሰጥተዋል፤ (1፡19፤ 2፡12፤ 3፡1-3 እና 14-18፤ 4፡11-12 ተመልከት)። ልብን ወይም የውስጥ አሳብን የሚገልጸው አንደበት ነው (ማቴ. 12፡34-35)። ልብ ትክክል ከሆነ ንግግርም ትክክል ይሆናል። የተገታ አንደበት ማለት በቁጥጥር ሥር የዋለ አካል ማለት ነው (3፡1-8)።

አገልግሎት (1፡27)፡- በቃሉ መስተዋትነት እራሳችንንና ከርስቶስን ካየን በኋላ ሌሎችንንና ችግራቸውን ማየት አለብን። ኢሳይያስ በመጀመሪያ ጌታን አየ፤ ቀጥሎ እራሱን አየ፤ ከዚያም ሊያገለግላቸው ያሉትን ሰዎች አየ (ኢሳይያስ 6፡1-8)። ቃላትን መናገር በራሱ ፍቅር ሊያደርገው የሚችለውን አያደርግም (ያዕቆብ 2፡14-18፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡11-18)። እግዚአብሔርን እኛ ራሳችን ማገልገል ሲገባን ሌሎችን በምትካችን ቀጥረን እንዲያገለግሉን ማድረግ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም።

ከዓለም መለየት (1፡27)፡- ያዕቆብ በዚህ ስፍራ «ዓለም» የሚለው ያለ እግዚአብሔር የሚኖረውን ጎብረተሰብ ነው። ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዥ ነው (ዮሐ. 14፡30)። የጠፉ ሰዎች የዚህ ዓለም ልጆች ናቸው (ሉቃስ 16፡8)። እንደ እግዚአብሔር ልጆች በሥጋ በዚህ ዓለም ብንሆንም እንኳ በመንፈስ ግን ከዚህ ዓለም አይደለንም። ሌሎችን ወደ ከርስቶስ እንድናመጣ ወደዚህ ዓለም ተልከናል (ዮሐንስ 17፡18)። ሌሎችን ማገልገል የምንችለው ከዓለም የመለየታችንን ውሳኔ እያጸናን ከሄድን ነው።

ዓለም ክርስቲያንን በማጥደፍ ልታረክሰው ትፈልጋለች። በመጀመሪያ፥ ከዓለም ጋር መወዳጀት ይጀምራል፥ (ያዕቆብ 4:4)፤ ይህም ዓለምን ወደ ማፍቀር ይመራል (1ኛ ዮሐንስ 2:15-17)። በጥንቃቄ ካልኖርን በስተቀር ይህን ዓለም እንመስላለን (ሮሜ 12:1-2)። ውጤቱም ከዓለም ጋር መኮነን ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 11:32)። ይህ ማለት ደኅንነታችንን እናጣለን ማለት አይደለም። የኖርንለትን ነገር ሁሉ ግን እናጣለን። ሎጥ የዚህ መሠረተ አሳብ ጥሩ ማስረጃ ነው። በመጀመሪያ ድንኳኑን ወደ ሶዶም አቅጣጫ ተከለ፤ ከዚያም ወደ ሰዶም ገባ፤ ብዙ ሳይቆይ ሰዶም ሁለንተናውን ወረሰና በቤተሰቡ መካከል እንኳ ምስክርነቱን አጣ። ፍርድ በሶዶም ላይ በመጣ ጊዜ ሎጥ የነበረውን ነገር ሁሉ አጣ። የዓለም ወዳጅ ከነበረው ከሎጥ ይልቅ ከዓለም የተለየው አማኝ፥ የእግዚአብሔር ወዳጅ የነበረው አብርሃም ለሕዝቡ ታላቅ አገልግሎትን ሰጥቷል። ክርስቲያን ዓለምን ለማገልገል በዓለማዊ ነገር ውስጥ የግድ መሳተፍ የለበትም። ኢየሱስ «እድፍ የሌለበት» (1ኛ ጴጥ. 1:19) ቢሆንም እንኳ የቀራጮችና ኃጢአተኞች ወዳጅ ነበር። ለዓለም አስፈላጊ አገልግሎት ለመስጠት ከሁሉም የተሻለ መንገድ ከዓለም ርኩሰት ፈጽሞ መንጻት ነው።